# አዲስ ዘመን

እንድ

ረቡዕ 82ኛ ዓመት ቁጥር 102 ታኅሣሥ 12 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ - በሐዱሽ አብርሃ

# አሳሳቢው የታዳጊዎች የፖስት ፒልና ቪያግራ መድኃኒቶች አጠቃቀም

**ጌትነት ተስፋማርያም**

ድንገተኛ ጽንስ እንዳይፈጠር የሚከላከለውን ፖስትፒል የተሰኘ መድኃኒት በየፋርማሲው በወረፋ ከሚቸበቸቡ መድኃኒቶች መካከል ከሆነ ሰንበትበት ብሏል። ቪያግራ የተሰኘውም ለስንፈተ ወሲብ ተብሎ የሚዘጋጅ መድኃኒትም ተማሪዎች ያለማንም ከልካይ ገዝተው ይጠቀማሉ።

በአዲስ አበባ የሚገኙ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አቅራቢያ በሚገኙ ፋርማሲዎች መድኃኒቶቹን አሁንም ለተማሪዎች በገሃድ ሲሸጡ ይስተዋላል።

የ13 ዓመቷ ሄራን ተስፋዬ (ስሟ የተቀየረ) ድንገተኛ ጽንስ እንዳይፈጠር የሚከላከለውን ፖስትፒል የተሰኘ መድኃኒት በአራት ወራት ውስጥ ለሶስት ጊዜ መውሰዷን ትናገራለች።

የአምስተኛ ክፍል ተማሪዋ ሄራን ጓደኛዬ ብዬ ከያዝኩት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ጋር በድብቅ እተኛለሁ፤ ደሞም ማርገዝ ስለሌለብኝ ከስጋት ለመዳን ስል ፖስትፒሉን ከፋርማሲ ገዝቼ እወስዳለሁ ስትል ሁኔታውን ታስረዳለች።

"በዚህ ዕድሜዬ ማድረግ ያልነበሩብኝን ነገሮች እያደረግኩ ነው፤ አዕምሮዬ ይጸጸታል። ይሁንና ቤተሰቦቼም ሆነ መምህሮቼ ጥፋቴን አያውቁም" ያለችው ሄራን፤ "ከዚህ ጉድ ሊያወጣኝ የሚችል የሥነልቦናም ሆነ የሕክምና እርዳታ አላገኘሁም። እኔም በሳምንት ለሁለት ቀናት ፖስት ፒሉን የወሰድኩበት ጊዜ ነበር" ትላለች።

ያለዕድሜያቸው ወደጾታዊ ግንኙነት የሚገቡና ያለሐኪም ትዕዛዝ ፖስትፒል መድኃኒትን በቀላሉ ገዝተው የሚጠቀሙ ተማሪዎች በርካታ ናቸው ስትልም ችግሩ የብዙዎች እንደሆነ ታስረዳለች።

"ትውልዱ ወዴት እያመራ ነው፤ በየቀኑ በአማካይ ደርዘን የሚደርስ የ11 ና የ12 ዓመት ሴት ተማሪዎች ወደፋርማሲያችን ይመጣሉ። ጥያቄያቸው ሁሉ ፖስትፒል ነው። መድኃኒቱን በ20 ብር ገዝተው ከወሰዱና ምክር

አሳሳቢው የታዳጊዎች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - በገባቦ ገብሬ

## "ጽንፈኝነት ለብሔርም ለሃገርም የማይበጅ እኩይ ተግባር ነው"

- አቶ ኢብሳ ነገዎ
የኦነግ ስትራቴጂ ጉዳዮች አማካሪ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ጽንፈኝነት ለየትኛውም ብሔርም ሆነ ለሃገር የማይበጅ አደገኛ አዝማሚያ በመሆኑ የጋራ ትግል ይጠይቃል ሲሉ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ስትራቴጂ ጉዳዮች አማካሪ አቶ ኢብሳ ነገዎ አስታወቁ፡፡

አቶ ኢብሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤

"ጽንፈኝነት ለብሔርም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በአማራ ክልል ከ235 ሺ በላይ ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው ተመልሰዋል

### - ከ600 ሺ. በላይ ተፈናቃዮች አሁንም ድጋፍ ይሻሉ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተፈረመውን ስምምነት ተከትሎ ከ235 ሺ. በላይ ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ መደረጉን የአማራ ክልል የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ በአሁኑ ሰዓትም ከ600ሺ. በላይ ተፈናቃዮች እንደሚገኙ አስታውቋል፡፡

የአማራ ክልል አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ኮሚሽን ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ እያሱ መስፍን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ላይ በተፈጸመው ሦስተኛ ዙር ወረራ ወቅት በክልሉ ከ850 ሺ. በላይ ተፈናቃዮች ነበሩ፡፡ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተፈረመውን ስምምነት ተከትሎ ከ235 ሺ. በላይ የሚሆኑት ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡

ከአጠቃላይ ተፈናቃዮች ውስጥ 250ሺ. የሚሆኑት በጦርነቱምክንያት የተፈናቀሉ መሆናቸውን አስታውሰው፤ ከ600 ሺ. በላይ የሚሆኑት ደግሞ ከአጎራባች ክልሎች በተለይም ከኦሮሚያና ቤንሻንጉል ጉሙዝ አካባቢዎች ተፈናቅለው የመጡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡



አቶ እያሱ መስፍን

እንደ አቶ እያሱ ገለጻ፤ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ማንነትን መሠረት ባደገረ ግጭት ከአጎራባች ክልሎች የተፈናቀሉ ከ600 ሺ. በላይ ዜጎች አሁንም በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ ይገኛሉ፡፡አሁን ላይም በምሥራቅ ወለጋ ባለው የሰላም እጦት ምክንያት 10 ሺ. የሚጠጉ ተፈናቃዮች ወደ ክልሉ መጥተዋል፡፡ አሁንም በርካታ ዜጎች በችግር ላይ ስለሚገኙ የእነዚህ ዜጎች ስቃይ

በአማራ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ‹‹የአሜሪካና አፍሪካ ግንኙነት ከፖሊሲ ሰጭና ተቀባይነት ወደ ስትራቴጂካዊ ግንኙነት እያደገ ነው››

- አቶ ቅዱስ ገዛኸኝ
የአፍሪካና እስያ ጉዳዮች ተመራማሪ

ገጽ 4

## ተቋሙ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃን ለማጥራት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ ነው

ገጽ 3













# ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋንን ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በ2030 በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁሉን አቀፍ የጤና ተደራሽነትን ለማሳካት በገባው ቃል መሠረት እንደ ሃገር እየሠራ መሆኑን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።ሚኒስቴሩ ከተለያዩ የሲቪክ ማኅበረሰብ ጋር በመሆን ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን ቀንን በትላንትናው ዕለት አክብሯል፡፡

የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ በዚሁ ወቅት ይህ መድረክ እየሠራን ያለነው ሥራ ምን ላይ ደረሰ፣ ምንስ ለውጥ ታየ የሚለውን የምናይበት እና ሁሉም መሪዎች ሥራቸውን የሚያጠናክሩበት መድረክ ነው ብለዋል፡፡

ሚኒስትሯ አክለውም መድረኩ ከሲቪክ ማኅበረሰቡ እና ከሌሎች አጋር አካሎች ጋር በመሆን መዘጋጀቱን ጠቁመው፤ ከሲቪክ ማኅበረሰቦቹ መካከል በዋናነት ሲሲዲኤ፣ ኮራ እና ሴቭ ዘቺልድረን ይገኙበታል ብለዋል። ይህም የሚያሳየው ልናሳካ ያሰበነውን የጤና ሽፋን ተደራሽነት መንግሥት ብቻ መሥራት የሚችለው ስላልሆነ በቅንጅት መሥራት እንደሚገባ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

ዶክተር ሊያ እንደተናገሩት እንደ ሀገር ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን ትኩረት የሚያደርገው በዋነኝነት የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አሃድን ማሳካት ላይ ነው ፡፡


ፎቶ - በእዮብ ተፈራ

ይህ ደግሞ ከጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራማችን ጀምሮ ጤና ጣቢያዎች እና የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የተጠናከረና የተሟላ አገልግሎት ወደ ማኅበረሰቡ ቅርብ ሆነው እንዲሰጡ ማድረግ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ሊያ ገለጻ አገልግሎትን እና ጤና ተቋማትን የማስፋፋት ሥራ ባለፉት ዓመታት በፌደራል መንግሥት ደረጃ ከክልል መንግሥታት ጋር በቅንጅት ሲሠራ ቆይቷል ።

ባለፉት ዓመታት ከተሠሩት ሥራዎችም የእናቶች እና የሕጻናት ጤና ፣ ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች መከሰትን መቀነስ ላይ ብዙ ውጤት ታይቷል። ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በአሁኑ ጊዜ እየተስፋፉ በመምጣታቸው በመጀመሪያ የጤና አሀድ ላይ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የመለየት፣የመመርመር እና ሕክምና የመስጠት ሥራ እየተሠራ ቢሆንም በሚፈለገው ልክ የጤና ሽፋን አለመዳረሱን ዶክተር ሊያ ገልጸዋል፡፡

ሚኒስትሯ አክለውም በቀጣይ በተለይ በግጭት የተጎዱ አካባቢዎችን በመደገፍ ቶሎ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል እየተሠራ ነው ብለዋል።ከዚህም ባለፈ ፍትሐዊ የተደራሽነት ችግር ያለባቸው ቦታዎች ላይ ትኩረት በማድረግ የጤና ተደራሽነትን በጥራት ለማስፋፋት አዲስ ፍኖተ ካርታ ለመተግበር እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል ፡፡

የሥነ ተዋልዶ ጤና ማኅበራት ጥምረት ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ዶክተር አበበ ከበደ በበኩላቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና ሌሎች የልማት አጋሮች ከመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት አንጻር ማንም ሰው ወደ ኋላ እንዳይቀር የመጨረሻ ግብ በማድረግ እየሠሩ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

# የሠራዊቱ አባላት በግዳጅ ቀጠናቸው ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የደረሱ ሰብሎችን ሰበሰቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-የ22ኛ ክፍለ ጦር የሠራዊት አባላት በግዳጅ ቀጠናቸው ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የደረሱ ሰብሎችን በመሰብሰብ የጉልበት ድጋፍ አደረጉ፡፡

የክፍለ ጦሩ ሥነ-ልቦና ግንባታ ቡድን መሪ ሻምበል አዲሱ አለማየሁ ድጋፉን አስመልክተው እንደገለፁት፤ ከራስ በፊት ለሕዝብ እና ለሀገር የሚለውን የተቋሙን እሴት በመላበስ ለኅብረተሰቡ የገንዘብና የጉልበት ድጋፍ እየተደረገ እንደሚገኝ አረጋግጠዋል።

ሻምበል አንተነህ ዳንኤል በበኩላቸው ሠራዊቱ እየፈፀመ ካለው ወቅታዊ ተልዕኮ ጎን ለጎን በግዳጅ ቀጠና ለሚገኙ አቅመ ደካሞች ሰብል በመሰብሰብ ድጋፍ መሳተፍ የሠራዊቱን ሕዝባዊነት ማሳየት ነው ብለዋል።

የሠራዊቱ የድል ሚስጥር ሕዝባዊነቱ በመሆኑ ከተረፈው ሳይሆን ካለው በማካፈል የገንዘብ ድጋፍ ከማድረጉም በተጨማሪ የተዘራ ሰብል ብክነት እንዳይደርስበት የመሰብሰብ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በሠራዊቱ የጉልበት ድጋፍ ከተደረገላቸው መካከል አቶ ዘውዱ መኮንን በሰጡት አስተያየት ፤ ሠራዊቱ ከዚህ በፊትም በችግራቸው ደራሽ እና ደጋፊ መሆኑን ገልፀው ፤



ለተደረገላቸው የጉልበት ድጋፍ አመስግነዋል ሲል የሀገር መከላከያ ሠራዊት በማኅበራዊ ገጹ ዘግቧል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከመደበኛ ተልዕኮው ጎን ለጎን በማንኛውም ጊዜ እና በየትኛውም ቦታ በሁሉም መስክ ለኅብረተሰቡ የሚያደርገው ያልተቆጠበ ድጋፍ የሕዝባዊነቱ መገለጫ መሆኑ ይታወቃል፡፡

# የቀበና ወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ ሊጀመር ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ሸገርን የማስዋብ ፕሮጀክት ምዕራፍ ሁለት አካል የሆነው የቀበና ወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ በያዝነው ዓመት እንደሚጀመር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ምክትል ኃላፊ እንዳሻው ከተማ (ኢንጂነር)፣ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ሸገርን የማስዋብ ፕሮጀክት ምዕራፍ ሁለት አካል ከሆኑት መካከል የሳይንስ ሙዚየም፣ የልጆች መጫወቻ እና የሰሥርግ ሥነሥርዓት ማከናወኛ ስፍራ ይገኙበታል፡፡

እነኝህ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ ያሉት ኢንጂነር እንዳሻው፤ የእነኝህ ፕሮጀክቶች አካል የሆነው የቀበና የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት በ2014 ዓ.ም ይጠናቀቃል ተብሎ ዕቅድ ቢያዝም በተለያዩ ምክንያቶች ዘግይቶ በያዝነው ዓመት ግንባታው እንደሚጀመር ታውቋል፡፡

ፕሮጀክቱ ከሦስት ዓመት በላይ ሲጓተት መቆየቱን አውስተው፤ በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ፣ የጨረታ ሂደቱ መራዘሙ፣ ሀገራችን ላይ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተያይዞ ተወዳዳሪ ተጫራቾች አለመገኘታቸውና ጨረታዎች በመሠረዛቸው ምክንያቶች ግንባታው ሊዘገይ መቻሉን አብራርተዋል።

በአሁኑ ጊዜም የጨረታና ዲዛይን ሥራው በመጠናቀቁና ሥራ ተቋራጭ በመለየቱ ከሦስት ወራት በኋላ ሙሉ ለሙሉ ግንባታው የሚጀመር መሆኑን ኢንጂነር እንዳሻው ተናግረዋል።

በሌላ በኩል፣ በኮሪያ መንግሥት ድጋፍ የሚገነባው የኮይካ የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክት በጥናት ላይ እንደሚገኝ አመልክተው፤ ጥናቱን በአጭር ጊዜ በማጠናቀቅ ወደ ግንባታ ለመግባት በጥረት ላይ እንገኛለን ብለዋል።

በአፍሪካ ልማት ባንክ ድጋፍ የሚገነባው ፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናቱ መጠናቀቁን ጠቁመው፤ በጥናቱ መሠረት ከኮይካ ፕሮጀክት ጋር በማጣጣም የዲዛይን ሂደቱን ለመጨረስና ወደ ትግበራ ለመግባት በሂደት ላይ እንደሚገኙም አመልክተዋል።

የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቱ አምስት ነጥብ አምስት ኪሎ ሜትር የሚረዝም መሆኑን ምክትል ቢሮ ኃላፊው ገልጸው፤ ይህም ከእንጦጦ ተነስቶ የጉለሌና አራዳ ክፍለ



ከተሞችን አልፎ ወዳጅነት አደባባይ ድረስ የሚሸፍን ነው ብለዋል።

ፕሮጀክቶቹ ከተማይቱን ውብና ጽዱ ከማድረግ ባሻገርም የመዝናኛ እና የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ እየተሠራ መሆኑን አመልክተው፤እነዚህ ፕሮጀክቶች የሚሠሩትም ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ጋር በጋራ መሆኑን ገልፀዋል።

የፕሮጀክቶቹ ዋና ዓላማ ወንዞቹን ውብና ፅዱ በማድረግ የማኅበረሰቡ መዝናኛ ማድረግ ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፣ ሥራው ሲጠናቀቅ ከማኅበረሰቡ የሚወጣ ፍሳሽና የሽንት ቤት ቆሻሻ ወደ ወንዙ እንዳይገባና እንዳይጣል እንደሚደረግም አስረድተዋል።

ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁም መሸጋገሪያ ድልድዮች፣ የስፖርት ማዕከላትና የብስክሌት መንገዶች እንደሚኖሯቸው ጠቅሰው፤ ፕሮጀክቶች ለከተማ ነዋሪዎቹ የተዋቡ የመዝናኛ ቦታ ከመሆናቸውም ባለፈ ለብዙ ወጣቶች የሥራ እድል እንደሚፈጥሩም ገልጸዋል።

እንደ ኢንጂነር እንዳሻው አገላለጽ፤ለቀበናው ፕሮጀክት ግንባታ የሚውል አምስት ሚሊዮን ዩሮ የጣሊያን መንግሥት ድጋፍ አድርጓል። በተጨማሪ ሙሉ በሙሉ የቴክኒክ እገዛ ይሰጣል። ፕሮጀክቱ ከሁለት ዓመት በኋላ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚታሰብም የቢሮው ምክትል ኃላፊ ጠቁመዋል።



ወይዘሪት ማርታ አድማስ

## ተቋሙ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃን ለማጥራት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ ነው

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በፌዴራልና በክልል የመንግሥት ተቋማት በሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ተቀጥረው የሚሠሩ ግለሰቦችን ለማጥራት በትብብር እየተሠራ መሆኑን የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ገለጸ።

የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ማርታ አድማስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ተቋሙ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃን ለማጥራት በሚሠራው መጠነ ሰፊ ሥራ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሠሩ ነው።

የፌዴራልና የክልል ተቋማት አዲስ የሰው ኃይል ቅጥር ሲፈፅሙ እና የደረጃ ዕድገት ሲሠጡ የሠራተኞችን የትምህርት ማስረጃ ሐሰተኛ መሆንና አለመሆኑ እንዲጣራላቸው ወደ ተቋሙ መላካቸው አብረው የመሥራት ቁርጠኝነታቸውን ያሳያል ብለዋል።

እንደማሳያም የደበብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከክልል እስከ ወረዳ ያለው የመንግሥት መዋቅር ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃን በማጋለጥና በማጥራት ሂደት ቀዳሚ እንደሆነ ገልፀዋል። በተጨማሪም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የጉምሩክ ኮሚሽን፣ ማዕከላዊ ስታስቲክስ እና ሌሎች የፌዴራልና የክልል ተቋማት ከትምህርት እና ሥልጠና ባለሥልጣን ጋር በቅርበት እየሠሩ መሆኑን ወይዘሪት ማርታ ተናግረዋል።

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃን ለማጥራት ተማሪዎች አገር አቀፍ ፈተና ወስደው የፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ያስቀመጠውን ከፍተኛ የግል ትምህርት ተቋም መግቢያ ነጥብ ማምጣታቸውንና መረጃ ተቀብሎ የማጥራት ሥራ እየሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የ12ኛ አገር አቀፍ ፈተና ወስደው ለከፍተኛ የመንግሥት ትምህርት ተቋም መግቢያ ነጥብ ያላመጡ ተማሪዎች በግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ገብተው እንዲሠለጥኑ የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣው የግል ተቋማት መግቢያ ነጥብ መኖሩን አውስተው ተማሪዎች የግል የትምህርት ተቋማትን ሲቀላቀሉ የፌደራል የትምህርት ሚኒስቴር ያወጣውን ነጥብ አሟልተው መግባታቸውን ለማጥራት የተማሪዎችን ሰነድ እየፈተሹ እንደሆነ አብራርተዋል።

አያይዘውም መስፈርቱን ሳያሟሉ በተገኙ ተማሪዎች እና ከተፈቀደላቸው የማስተማር፣ የፕሮግራም እና የቁጥር ፍቃድ ውጭ እየተቀበሉ በሚያሠለጥኑ የግል ተቋማት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ መረጃ በማሰባሰብ ላይ መሆኑን ገልፀዋል። በተጨማሪም የግል ተቋማት በአንድ የሙያ ዘርፍ ከተፈቀደላቸው የተማሪ ቁጥር በላይ አልፈው ሲያሰለጥኑ ከተገኙ ተማሪዎች ብቻ መቀጣታቸው ቀርቶ ተቋማትንም ለመቅጣት ከፍትሕ አካላትና ከፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ጋር ለመሥራት መታቀዱን ገልፀዋል።

በተጨማሪም ተቋሙ የማስተማር ፍቃድ እና የሚሰጣቸው የፕሮግራም ፍቃድ የማጣራት ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ጠቁመው፤ ለኅብረተሰቡም ስለጉዳዩ ግንዛቤ እንዲኖረው ማንኛውንም የሚዲያ አውታር በመጠቀም ግንዛቤ እንዳስጨበጠና በማስጨበጥ ላይ እንደሆነ የባለስልጣኑ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ተናግረዋል።

ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃን ለማጥራት የፌዴራል መንግሥት በተለያየ ዘርፍ ከባለሥልጣኑ ጋር እየሠራ መሆኑን እና ወደፊትም በቁርጠኝነት ለመሥራት ጥናት እየተደረገ እንደሆን ጠቁመው ትውልድ ገዳይ የሆነውን ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ለማጥራት መንግሥት፣ ኅብረተሰቡ እና ሚዲያዎች በማጋለጥ የበኩላቸውን እንዲወጡ መልክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ሥራ አጥነት አሻፈረን ያሉ ወጣቶች

**ቃልኪዳን አሳዬ**

በሀገራችን ኢትዮጵያ በየዓመቱ ከግልና ከመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ከ2ሺ በላይ ወጣቶች እንደሚመረቁ የትምህርት ሚኒስቴር መረጃዎች ያመለክታሉ። ታዲያ እነኝህን ወጣቶች ተቀብሎ ወደ ሥራ ለማስገባት የመንግሥት አቅም አነስተኛ እንደሆነ ይታወቃል። ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ የመጣው የሰው ኃይል ቁጥር ከመንግሥትም ሆነ ከግሉ ዘርፍ መፍትሔ የሚሻ አንገብጋቢ ጉዳይ እንደሆነ እስካሁን ቀጥሏል።

ነገር ግን ሥራ አጥነት አሻፈረን ትርፉ ብክነት ነው ያሉ ወጣቶች በተማሩበት እና ባላቸው ዝንባሌ መሠረት የተለያዩ ሥራዎችን በመፍጠር ለሀገርና ለሕዝብ ከዚያም አለፍ ሲል ለራሳቸውም ኩራት በመሆን ላይ ይገኛሉ። ለዚህም ማሳያ እንዲሆን ይዘን የቀረብነው በቦሌ ክፍለ ከተማ ቢዩ (ራስህን ሁን) ዴልቬሪ ሰርቪስ በሚል ተደራጅተው ሥራ የፈጠሩ ወጣቶችን ነው።እነኝህ ወጣቶች በዋናነት በኢንጂነሪንግ የትምህርት መስክና በመሳሰሉ የትምህርት ዓይነቶች የመጀመሪያ ዲግሪ የያዙ ወጣቶች ናቸው። በውጪ ሀገር ዜጎች አነሳሽነት ስልጠና በመውሰድ ሥራቸውን እንደጀመሩ ይናገራሉ።

የቢዩ ዴልቬሪ ሰርቪስ የቢዝነስ ልማት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ብሩክ ገነነ እንደሚሉት ይህ ተቋም ከተመሠረተ አንድ ዓመት ከሦስት ወር አልፎታል በዋንኛነት በዚህ ድርጅት የሚሠሩ ሥራዎች ከደንበኞች ትዕዛዝ በመቀበል ከተለያዩ ሬስቶራንቶች የፈለጉትን አይነት ምግብ ማድረስ ነው። ይህ ሥራ የሚከናወነው ሞተረኞችን በመጠቀም ነው። ምንም እንኳን በጅምር ላይ ብንገኝም በሥራችን ሦስት መቶ ሞተረኞች አሉን፤ በቅርቡ ለሴቶች ልዩ ዕድል ለመፍጠር በማሰብ ሃምሳ ሴት ሞተረኞች አሰልጥነን ወደ ድርጅታችን ቀላቅለናል። ባጠቃላይ ከእኛም አልፈን 350 ለሚደርሱ ወጣት ሞተረኞች ሥራ መፍጠር ችለናል ይላሉ አቶ ብሩክ።

ለማሳያነት እንኳን በዚህ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራው መለሰ ስንታየሁ ስለ ሥራ ሕይወቱና ወደፊት ለመሥራት ስላቀዳቸው ጉዳዮች እንዲህ ይላል "ከቢዩ ጋር መሥራት የጀመርኩት በሹፍርና ነበረ፤ አሁን ላይም በዚሁ ድርጅት ውስጥ እየሠራሁ ጎን ለጎን እራሴን ለመቀየር እጥራለሁ። ሥራውን ስጀምር የተመደብኩት ከባድ ዳገትና ቁልቁለት ያለበት ቦታ ላይ ነው። ብዙ የተለያዩ ችግሮች ገጥመውኛል፤ ዓላማ ስላለኝ እነዛን ችግሮች አልፌ እዚህ ደረጃ ላይ ደርሻለሁ።



አቶ ብሩክ ገነነ



ወጣት መለሰ ስንታየሁ

እነዛ የተለያዩ ችግሮችን አልፌ የራሴን አነስተኛ ሬስቶራንት ከፍቻለሁ። ጎን ለጎን አሁንም በዚሁ ድርጅት ላይ እያገለገልኩ ነው። ከዚህ ቀደም እሠራበት ከነበረው ከፍ ብዬ የአሽከርካሪዎች ቡድን መሪ ሆኛለሁ። ትልቅ ዓላማ አለኝ ባለ አምስት ኮከብ ሆቴል የመክፈት ዓላማ አለኝ፤ ወደፊት ያም እንደሚሳካ እርግጠኛ ነኝ፤ ያንን ለማሳካት አሁን ላይ ተግቼ እየሠራሁ ነው። ሰው ዓላማ ይዞ ከተነሳ ምንም ነገር ሊያግደው አይችልም። ሁሌም ቢሆን በሕይወት ላይ ፈተና አለ፤ ነገር ግን ዋናው ነገር ተቋቁሞ ማለፍ ነው ብሏል፡፡

ይህ ድርጅት ከተለያዩ ደንበኞቹ በቀን 2000 የሚደርሱ ትዕዛዞችን በመቀበል ከ700 በላይ ከሚሆኑ ሬስቶራንቶች ጋር ስምምነት በመፈጸም ምግቦችን ወደ ተመዝጋቢዎች በያሉበት ያደርስላቸዋል። ነገር ግን ትዕዛዞቹን ሁሉ በሚያደርሱበት ወቅት የተለያዩ ችግሮች ይገጥማቸዋል። ከእነዚህም መካከል ከሬስቶራንቶቹ ዘንድ የምግብ መዘግየት፣ የሞተረኞቹ በሰዓት አለመገኘት፣ ትዕዛዝን በመቀበልና በማድረስ ጊዜ ውስጥ የጊዜ ብክነት፣ የምግብ ጥራት ማነስ፣ የደንበኞች ሀሳብ የመቀየርና የመሳሰሉ ናቸው። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ድርጅቱ ዘዴ ዘይዷል። ትዕዛዝ በመቀበልና በማድረስ የሚባክነውን ጊዜ ለመቀነስ አዲስ መተግበሪያ ይፋ አድርጓል። ታድያ ይህ መተግበሪያ በፍጥነት ከደንበኞች ትዕዛዝን በመቀበል ወደ ሬስቶራንቶች በማድረስ ጊዜን ይቆጥባል።

እንደ አቶ ብሩክ ገለጻ፤ "አገልግሎቶቹን የምንሰጠው ከትንንሽ ቤቶች ጀምረን እስከ ትላልቅ ሬስቶራንቶችና ሆቴሎች ድረስ ነው" እነኝህ ወጣቶች የመሠረቱት ድርጅት ምንም እንኳን ዕድሜው ገና ሆኖ መነሻውን ኢትዮጵያ ቢያደርግም በመጪዎቹ ሁለት ዓመታት ውስጥ በ15 የአፍሪካ ሀገራት ሥራውን ለማስፋት አቅዶ በትኩረት እየሠራበት ይገኛል። ለዚህም ማሳያ እንዲሆን በቅርቡ በታንዛኒያና አንጎላ ሥራ ጀምሯል። ይህ ድርጅት ለወደፊትም የምግብ ጥራት እና ፈጣን ተደራሽነትን በመጨመር በአፍሪካ ትልቁ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ የመሆን ፍላጎት እንዳለው ሥራ አስኪያጁ አመላክተዋል።

የሥራ እድል የተፈጠረላቸው ወጣቶች አብዛኞቹ ሰፈር ላይ የሚቀመጡ ናቸው። አሁን ላይ በተሻለ መልኩ ለተጨማሪ ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በትኩረት እየሠራን ነው ፤በቅርቡ ከቦሌ ክፍለ ከተማ ጋር በመነጋገር ሥራው ላይ ተሠማርተው መሥራት እየፈለጉ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ወደኋላ እየተመለሱ ያሉ ወጣቶች አሉ፤ ይህን ችግር ለመቅረፍ ከክፍለ ከተማው ጋር ተነጋግረን ብድር እያመቻቸን እንገኛለን ብለዋል።

በሀገራችን እየታየ ያለውን ገደብ የለሽ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ የመንግሥትም ሆነ የግሉ ዘርፍ ሊረባረብ የግድ ይላል። የሥራ ፈጣሪዎችን በማበረታታት የሥራ አጥነትን ከመቀነስ አኳያ መንግሥት እንዲህ አይነት ወጣቶችን ሊያበረታታና የሚያስፈልገውን ድጋፍ በመስጠት ለሌሎች ወጣቶች አርአያ እንዲሆኑ በትኩረት ሊሠራበት እንደሚገባ ወጣቶቹ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

# ትላልቅ ተቋራጮች ከአነስተኞች ጋር በጥምረት እንዲሠሩ የሚያደርግ አስገዳጅ ሕግ ሊወጣ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚታዩ ክፍተቶችን ለማረም በሀገሪቱ የሚገኙ ትላልቅና ዋና ዋና ተቋራጮች ከትናንሽ ተቋራጮች ጋር በጥምረት እንዲሠሩ ለማስቻል በሕግ አስገዳጅ ተደርጎ ሊወጣ እንደሆነ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ገለጸ፡፡

የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ዳዊት መሐሪ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከደረጃ አንድ እስከ ዘጠኝ የተመዘገቡ ኮንትራክተሮች 4 ሺህ 448 ያህል ናቸው።ሆኖም ትናንሽ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋራጮች በሚገባው ልክ እያደጉ አለመሆናቸው በዘርፉ ላይ የሚታዩ ክፍተቶች እንዲሰፉ አድርጓል።

በአሁኑ ጊዜ ያለው አሠራር የትናንሽ ተቋራጮችን የማደግ ዕድል ያጠበበ ከመሆኑም በላይ በዘርፉ የሚኖረውን የዕውቀት ሽግግር ዝቅተኛ አድርጎታል።በመሆኑም እየተስተዋሉ ያሉ መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ ትላልቅ ተቋራጮች ከትናንሽ ተቋራጮች ጋር እንዲሠሩ የሚያስገድድ ሕግ ተግባራዊ ለማድረግ በሂደት ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

አስገዳጅ ሕጉ ተግባራዊ ሲደረግ ትላልቅ የኮንስትራክሽን ተቋራጮች የሥራውን የተወሰነ ክፍል ለትናንሽ ተቋራጮች እንዲሰጡ ይገደዳሉ ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ ይህ መሆኑ ትናንሽ ተቋራጮች ልምዳቸውን እያዳበሩ የማደግ ዕድል



እንደሚፈጥርላቸው እና አዳዲስ ከፍተኛ የሥራ ተቋራጮች እንዲፈጠሩ እንደሚያደርግ አብራርተዋል።

እንደ አቶ ዳዊት ገለፃ፤ የትናንሽ እና የትላልቅ ተቋራጭ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች የግንኙነት አግባብ በሕግ ማዕቀፍ ባለመቀንበቡ፤ በመካከላቸው ለሚፈጠር የክፍያና መሰል ውዝግብ ሕጋዊ የሆነ የመፍቻ ሥርዓት የለም። ይህ አስገዳጅ ሕግ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ ግን ሁለቱም ተቋራጮች በሕግ አግባብ የሚስተናገዱበት ድንጋጌ የሚያካትት በመሆኑ አለመግባባቶችን በመፍታት እና አብሮ ለመሥራት ጠቀሜታ አለው፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ በኮንስትራክሽኑ ዘርፍ ያሉ ክፍተቶች ጥናት መካሄዱንና ዋና ዋና የሚባሉ የዘርፉ ክፍተቶች መለየታቸውንም አቶ ዳዊት አክለው ተናግረዋል፡፡

የኮንስትራክሽን ዘርፉ ላይ ያሉትን ችግሮች ያነሱት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ ከስር ላሉት ተቋራጮች የሥራ ዕድል የማግኘት ችግሮችን ብቻ ሳይሆን ብዙ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እና ወጪ ያለማለቅ ችግር እና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ይዞ ለሚመጣ ተቋራጭ ለይቶ የሚያበረታታ ሥርዓት አለመኖሩን ለአብነት አንስተዋል።

በጥናት የተለዩ ችግሮች ለመቅረፍም የወደፊት የኮንስትራክሽን ዘርፉን ማሳደግና መለወጥ የሚችሉ የመፍትሔ አቅጣጫዎች መቀመጡን አብራርተዋል፡፡

በዚህም ትናንሽ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋራጮች ለማሳደግ ከዋና ዋና እና ትላልቅ ተቋራጮች ጋር በጥምረት የሚሠሩበትን መንገድ መፍጠር አንዱ መሆኑን አስታውሰው፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ይዘው የሚመጡ ኮንትራክተሮች የሚበረታቱበትን አሠራር ማስጀመር አንዱ እንደሆነ ተናግረዋል።

በተጨማሪም በዘርፉ በተደረጉ ጥናቶች ከዚህ በፊት በሀገሪቱ ያልተለመዱ አዳዲስ አሠራሮችን ለማስጀመር መታቀዱን የገለፁ ሲሆን፤ እንደ አብነትም “አርክቴክቸራል እንጂነሪንግ ፕሮዳክቲቪቲ ኖርም” የሚባለውንና ሕንፃዎች ሲሠሩ ምን ያህል የጊዜ ገደብ መሰጠት አለበት ለሚለው መረጃ የሚሰጠው አሠራር በቅርቡ እንደሚጀመር ጠቅሰዋል፡፡

# ባለፉት 5 ወራት ከቡና ወጪ ንግድ ከ615 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አምስት ወራት ለውጭ ገበያ ከቀረበ የቡና ምርት ከ615 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ገለጸ።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የግብይት ዘርፍ ኃላፊ ሻፊ ዑመር ባለፉት አምስት ወራት ለውጭ ገበያ ከ109 ሺህ ቶን በላይ የቡና ምርት እንደቀረበ ተናግረዋል፡፡

በዚህም የቡና ምርት 615 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን ተናግረው ፣ ገቢው ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ100 ሚሊዮን ዶላር ብልጫ እንዳለው አንስተዋል፡፡

የቡና ምርቱ ከተላከባቸው ሀገራት መካከል ጀርመን፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ ቤልጂየም፣ አውስትራሊያና ጃፓን እንደሚገኙበትም ገልጸዋል።

የገበያ መዳረሻዎቹን በማስፋት ዘንድሮ ወደ ቻይና እና ኢንዶኔዥያ ቡና የመላክ ሥራ መጀመሩንና ይህም ለገቢው መጨመር ጉልህ አስተዋፅኦ ማበርከቱን ተናግረዋል።

በዘንድሮ በጀት ዓመት 360 ሺህ ቶን ቡና በመላክ እስከ 2 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

የውጭ ንግድን በገቢ ከማሳደግ አኳያ የቡና ኤክስፖርት ከአምራች እስከ መዳረሻ ገበያ በማስተባበር፣ በመከታተል፣ በመደገፍና በማምረት ባለፈው ዓመት በመጀመሪያ ስድስት ወራት ከ139 ቶን በላይ ቡና በመላክ 525 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱ የሚታወስ ነው።

የቡና ኤክስፖርት በመጠንና ገቢ እንዲያድግ የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት እንደሚያስፈልግ መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት አሳስቧል።



በቡና ምርት ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውጤት እንዲኖራት በማድረግ አስተዋጽኦ ላደረጉ የቡና አምራች አርሶ አደሮች፣ ላኪዎች እና አቅራቢዎች የእውቅና አሰጣጥ መርሐ ግብር በ2015 ዓ.ም መጀመሪያ ተካሂዷል።

በወቅቱ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ300 ሺሕ ቶን በላይ ቡና ወደ ውጭ በመላክ አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ማግኘቷ ተገልጿል።

## አሳሳቢው የታዳጊዎች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከሰጠናቸው በኋላም በሳምንታቸው ተመልሰው የሚመጡ አሉ" የምትለው ደግሞ አራት ኪሎ በሚገኝ ፋርማሲ የምትሠራው እድላዊት ጌትነት ነች።

በቅርቡ በግምት 12 ዓመት የሚሆናት ተማሪ ፖስትፒል ልትገዛ መጣች። በዚህ ዕድሜዋ መማር ሲገባት አላስፈላጊ የወሲብ ግንኙነት ማድረጓ አግባብ እንዳልሆነና የወደፊት ሕይወቷን ሊያበላሽ የሚችል ችግር እንደሆነ መክሬ ከነመድኃኒቱ ሸኘኋት ስትል ባለሙያዋ ያጋጠማትን አጋርታለች።

ተማሪዎቹ መድኃኒቶቹን ሲገዙ በተቻለ መጠን የዜግነት ኃላፊነታችንን ለመወጣት ምክር እንለግሳቸዋለን፤ ችግሩ ግን በግለሰቦች ምክርና ተግሳጽ ብቻ አይቆምም። በትምህርት ቤቶች አካባቢ ጠንከር ያለ ቁጥጥርና ርምጃ ይጠይቃል። ያለበለዚያ ግን ትውልድ እያጣን ነው ስትል ስጋቷን ገልጻለች።

ከሴት ተማሪዎች ባለፈ ወንድ ተማሪዎችም ቪያግዛ የተሰኘውን የስንፈተ ወሲብ መድኃኒት ይጠይቃሉ። መድኃኒቱ ያለሐኪም ትዕዛዝ የማይሸጥ በመሆኑ ባናቀርብላቸውም በተለያዩ ፋርማሲዎች ግን በቀላሉ ይገኛል ስትል ትዝብቷን አጋርታለች።

ፖስትፒልን እኛም መደብር በብዛት የሚገዙት ተማሪዎች ናቸው የምትለው መገናኛ አካባቢ በሚገኝ ፋርማሲ የምትሠራው ሰላማዊት አሸናፊ (ስሟ የተቀየረ) ነች። ከፖስትፒል ባለፈ ተማሪዎች ቪያግራ የተሰኘውን መድኃኒትም ይጠቀማሉ ስትል ተናግራለች።

መድሃኒቱ ከፖስትፒል በተለየ ሁኔታ ካለሐኪም ትዕዛዝ አይሸጥም፤ ይሁንና እናንተ ለምን ለተማሪዎቹ ትሸጣላችሁ የሚል ጥያቄ ያነሳሁላት ባለሙያዋ መልሷ ግን ዝምታ ብቻ ነበር። ጥፋተኝነቷ ቢገባትም ትውልድ እየገደሉ እንደሆነ ብትረዳም፤ አንገት ከማቀርቀር ያለፈ መፍትሔ ግን አልነበራትም።

በአቅራቢያው በሚገኙ ፋርማሲዎች ቪያግራ የተሰኘውን በዘፈቀደ ያለሐኪም ማዘዣ የሚቀርብላቸው በመሆኑ ተማሪዎቹ ባሻቸው ሰዓት መጥተው እንደሚገዙ አረጋገጥኩ።

ጥያቄዎቼን በዋናነት ወደሚመለከተው ተቋም ወደኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን አቀረብኩ።

በባለስልጣኑ የመድኃኒት ተቋማት ኢንስፔክሽን ረዳት ዳይሬክተር አቶ መንግስቱ እንዳለው፤ ፖስትፒል ያለሐኪም ትዕዛዝ ቢሸጥም ባለሙያዎች ምክር እየሰጡ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፤ ቪያግራ ግን ፈጽሞ ያለማዘዣ የማይሸጥ በመሆኑ ችግሩ ሲገኝ ፋርማሲዎች ላይ ቅጣት እንደሚጣል ነው የሚያስረዱት።

እስከዛሬ ምን ያክሉ ላይ ርምጃ ተወሰደ ለሚለው ትክክለኛ አኃዝ ባያቀርቡም፤ ፋርማሲዎቹ ላይ ቁጥጥር በማድረግ ከማስጠንቀቂያ ጀምሮ ንግዳቸውን እስከማዘጋት የሚደርስ ርምጃ እንደሚወሰድ ነው የገለጹት።

በትምህርት ቤት አቅራቢያ የሚገኙ ፋርማሲዎች በተለየ መልኩ ለተማሪዎች የማይሆኑ መድኃኒቶችን ከማቅረብ ሊቆጠቡ እንደሚገባም በመግለጽ፤ የፋርማሲ ባለሙያዎችም ሙያዊ ግዴታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ማሳሰቢያ አዘል መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የእናቶችና ሕፃናት ሐኪሙ ዶክተር ሔኖክ አሸናፊ በበኩላቸው፤ ፖስትፒልም ሆነ ቪያግዛ መድኃኒቶችን ተማሪዎች በተደጋጋሚ መውሰዳቸው አደጋ አለው ይላሉ።

ሴቶች ለድንገተኛ ጊዜ ብቻ የሚውለውን የጽንስ መከላከያ ፖስትፒል በተደጋጋሚ የሚወስዱ ከሆነ በመጨረሻ ለመሐንነትም ጭምር የሚያጋልጥ ችግር ሊደርስባቸው እንደሚችል ነው የሚያስረዱት።

ቪያግራ ደግሞ ለስንፈተ ወሲብ የሚሰጥና በሐኪም ትዕዛዝ ብቻ መሸጥ ያለበት ነው። ምክንያቱም መድኃኒቱ የደም ቧንቧን የሚያሰፋና ከደምና ልብ ጋር በተያያዘ ግንኙነት ያለው በመሆኑ ካልተፈቀደለት ሰው ውጪ ሲወስደው ለውስብስብ የጤና ችግር እንደሚያጋልጥ ይገልጻሉ።

ዶክተር ሔኖክ እንደሚያስታወቁት፤ በመድኃኒቶቹ የተነሳ ተማሪዎቹ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ በፋርማሲ ባለሙያዎች፣ በተማሪዎቹና በሚመለከታቸው አካላት በኩል የሚደረገው ጥንቃቄ ሁሉ ከፍ ሊል ይገባል። የትምህርት ተቋማት በአልባሌ ጉዳዮች ከመጠመድ ይልቅ ተማሪዎቹ ላይ ቁጥጥሩን ማጠናከር ይኖርባቸዋል።

## ‹‹የአሜሪካና አፍሪካ ግንኙነት ከፖሊሲ ሰጭና ተቀባይነት ወደ ስትራቴጂካዊ ግንኙነት እያደገ ነው››

- አቶ ቅዱስ ገዛኸኝ
የአፍሪካና እስያ ጉዳዮች ተመራማሪ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የአሜሪካና አፍሪካ ግንኙነት ከፖሊሲ ሰጭና ተቀባይነት ወደ ወንድማማችነት መንፈስና ስትራቴጂካዊ ግንኙነት እየተቀየረ መሆኑን የአፍሪካና እስያ ጉዳዮች ተመራማሪ አቶ ቅዱስ ገዛኸኝ አስታወቁ፡፡

የአፍሪካና እስያ ጉዳዮች ተመራማሪ አቶ ቅዱስ ገዛኸኝ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ አሜሪካ ከአፍሪካ ጋር የነበራት ግንኙነት የፖሊሲ ሰጭና ተቀባይነት ግንኙነት ነበር። አሁን ባለው ሁኔታ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኃያላን ሀገራት እየተበራከቱ መምጣት አሜሪካ ለአፍሪካ ያላትን እይታ እንድትቀይር አስገድዷል።ከፖሊሲ ሰጭነት ወደ እኩልነት፣ የወንድማማችነት መንፈስና ስትራቴጂክ ግንኙነት ተቀይሯል።

በቻይና ከመቀማቷ በፊት በአፍሪካ ሀገራት ትልቁ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የአሜሪካ ነበር፤ ይህም ጠንካራ ግንኙነት መኖሩን ያመላክታል።አሁንም አሜሪካ በአፍሪካ ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ላይ በስፋት ለመሠማራት ፍላጎት አላት ብለዋል፡፡

እንደ ተመራማሪው ማብራሪያ፤ ውስጣዊ አንድነቶችን በማጠናከርና፣ የውስጥ መረጋጋትን ከመቼውም ጊዜ በላይ በመፍጠር በኢኮኖሚ ላይ የተመሠረተ እድገት ማምጣት ከተቻለ አሜሪካ ከአፍሪካ ጋር መልካም ግንኙነት ይኖራታል። ውስጣዊ መረጋጋት ከሌለ ግንኙነቶች ሁሌም በአሜሪካ ፖሊሲ ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ ይሆናሉ ሲሉም አክለዋል።

በአፍሪካ የወጣቶች ብዛትና የተማረ የሰው ኃይል ማደግ አሜሪካ ፖሊሲ ጫኝ፤ አፍሪካ ፖሊሲ ተቀባይ የምትሆንበት ጊዜ እያበቃ ነው ያሉት ተመራማሪው፤ ከዚህ በኋላ ግን ግንኙነቱ እየተሻሻለ ይመጣል ብለዋል። በዘላቂነት የተሻለ ግንኙነት እንዲኖር አፍሪካ የውስጥ የቤት ሥራዋን መሥራት አለባት፤ መልካም ግንኙነት የሚፈጠረው በአሜሪካ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በአፍሪካውያን ጥንካሬ ላይ መሆን መቻል አለበት ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ቅዱስ ገለጻ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአፍሪካ የተማረ የሰው ኃይል ቁጥር መጨመር፣ አንዳንድ የአፍሪካ አገራት በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ መግባት፣ አንጻራዊ የዲሞክራሲ እድገት መኖር የአፍሪካ አህጉር የአሜሪካን ፖሊሲ ከመቀበል ወደ ስትራቴጂካዊ ግንኙነት ለውጦታል። የተማረ የሰው ኃይል በብዛት እና በጥራት መኖሩ የአገርን ጉዳይ ከውጭም ይሁን ከውስጥ በጥልቀት ማየት ይችላል፤ ይህም አፍሪካ ከሌሎች አህጉራት ጋር ያላትን ግንኙነት እያስተካከለው መጥቷል ሲሉም ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ የአፍሪካ ትልቁ ሀብቷ የሰው ኃይል ነው፤ በተለይ የተማረው የሰው ኃይል የእውቀት ሽግግርን በማምጣት የኢንዱስትሪ ዘርፉን ያሳድጋል። ይህም አሜሪካ በአፍሪካ ያላትን የፖሊሲ እይታ እንድታስተካክል በማድረግ እኩል ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ ግንኙነት እውን እየሆነ መምጣቱን ያሳያል ሲሉም አብራርተዋል፡፡

አሜሪካ በአፍሪካ የሰብዓዊ ድጋፍ በማድረግ ከዓለም ቀዳሚ አገር ናት ያሉት ተመራማሪው፤ በየዓመቱ አስራ አንድ ቢሊዮን ዶላር ትሰጣለች፤ በአሜሪካ-አፍሪካ ግንኙነት የአሜሪካ ፍላጎት ኢንቨስትመንት ማካሄድ ነው፤ አፍሪካም ለዚህ የሚመጥን ፖሊሲ በማዘጋጀት በቀጥታ በውጭ ኢንቨስትመንት እንዳደጉት የእስያ ሀገራት ማደግ ትችላለች ብለዋል።

አሜሪካና ቻይና ወደ አፍሪካ ሲመጡ የራሳቸውን ፍላጎት ይዘው ነው የሚመጡት።ሁለቱም የራሳቸው የሆነ ፍላጎት አላቸው፤ አፍሪካም በበኩሏ ከአሜሪካና ከቻይና ጋር የሚኖራት ግንኙነት ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን የራሷን የፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ መቅረጽ አለባት ሲሉም ተንታኙ ተናግረዋል፡፡

## “ጽንፈኝነት ለብሔርም...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለውጡን በኃይል በመቀልበስ ሥልጣን ለመያዝ በሚፈልጉ ኃይሎች አገር ዋጋ እየከፈለች ትገኛለች።በተለይ በኦሮሚያ ክልል የሚንቀሳቀሱ የሸኔ ታጣቂዎች በለውጡ ማግስት አፈንግጠው በመውጣት ትግል በመጀመር በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳት እያደረሱ ይገኛሉ።በተመሳሳይ መልኩ በሌሎች አካባቢዎችም ምኞታቸውን በሕዝብ ላይ በኃይል ለመጫን የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኛ ኃይሎች ይገኛሉ፡፡

በዚህች ላይ አገር ብሔርን ተገን በማድረግ ሥልጣንን በኃይል ለመቆናጠጥ የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኛ ኃይሎች በመጀመሪያ ለብሔራቸው ሲቀጥል ደግሞ ለሀገር ራስ ምታት መሆናቸውን አውስተዋል።

ከማንኛውም አካባቢ የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኛ ኃይሎች በስም እንጂ በተግባር አንድ መሆናቸውን ያብራሩት አማካሪው፤ አንደኛው ሃገር እንዳትረጋጋ ትኩረት ለመሳብ ንጹሓን ዜጎች ላይ እርምጃ ሲወስድ፤ሌላው ነገሩን ይበልጥ በማክረር ከመጠን በላይ ያስተጋባለታል፤ አሊያም እሱም ድንበር ዘሎ ተመሳሳይ እርምጃ በመውሰድ የጥፋቱ ተባባሪ ለመሆን ይጥራል ብለዋል።

ሁሉም ጽንፈኛ ኃይሎች በንጹሓን ዜጎች ላይ ዘግናኝ እርምጃ ከመውሰድ በዘለለ በብልጽግና ፓርቲ ውስጥ ጥሩ መስተጋብር ባላቸው የኦሮሞና የአማራ ባለሥልጣናት መካከል ጥርጣሬና ያለመተማመን ለመፍጠር የሚያደርጉት ጥረት ቀላል አይደለም ያሉት አቶ ኢብሳ፤ ይሄን ዘዴ የሚጠቀሙት በኃይልና ሥልጣን መቆናጠጥ እንደማይታሰብ በደንብ ስለሚያውቁ በሴራ ምኞታቸውን ለማሳካት በማመን ጭምር መሆኑን አስገንዝበዋል።

ሁለቱን ታላላቅ ብሔሮች ለማጋጨት ጽንፈኞች ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም ያሉት አቶ ኢብሳ፤ ነገር ግን አንዳንዶች ሴራውን በብስለትና በሰከነ መንፈስ ማምከን ሲገባቸው የጽንፈኞቹን አጀንዳ የማስተጋባት አዝማሚያ ይስተዋላል ይሄ ደግሞ ሊስተካከል የሚገባው ነው ሲሉ ሀሳባቸውን ቋጭተዋል።

## በአማራ ክልል...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንዲያበቃ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ይጠይቃል ብለዋል፡፡

በክልሉ ለ8 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዜጎች እርዳታ ተጠይቆ እንደነበር ጠቅሰው፤ በመጀመሪያው ዙር የተፈቀደው ለ5 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዜጎች፣ በሁለተኛው ዙርም በ156 ወረዳዎች ከ5 ነጥብ 6 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ድጋፍ ቀርቦ ተሰራጭቷል ብለዋል፡፡

ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ወለጋ ዞን ለተፈናቀሉ ዜጎች የሚውልም ከፌዴራል መንግሥት 100 ኩንታል፣ ከክልሉ መጠባበቂያ ላይም 300 ኩንታል ወጭ ተደርጎ ተፈናቃዮቹ ወደሚገኙባቸው አካባቢዎች መላኩንም አቶ እያሱ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ሰላሙ አስተማማኝ ካልሆነ አሁንም የሚፈናቀሉ ዜጎች መጨመሩ አይቀርም ያሉት አቶ እያሱ፤ ይህን መሠረት ያደረገ ምግብ ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች መቅረብ አለባቸው።በመሆኑም መንግሥት ከሚያደርገው ድጋፍ ጎን ለጎን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሕዝቡም የበኩሉን ድጋፍ ማድረግ አለበት ብለዋል፡፡

መንግሥትና ማኅበረሰቡ ባደረጉት ጥረት እስካሁን የከፋ ችግር እንዳይደርስ መደረጉን የጠቆሙት አቶ እያሱ፤ ድጋፉ በወቅቱ አለመምጣት፣ በተጠየቀው ልክ አለመሆንና የእናቶችና ሕጻናት አልሚ ምግብ ተሟልቶ አለመቅረብ ድጋፉን የተሟላ እንዳይሆን አድርጎታል ብለዋል፡፡

መንግሥት ከሚያደርገው ድጋፍ ባለፈ አመልድ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ድጋፍ ለማድረግ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ጠቁመው፤ ሌሎች ግብረ ሰናይ ድርጅቶችም አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል፡፡

በክልሉ ከሚገኙ አጠቃላይ ተፈናቃዮች ውስጥ 68 ሺ 445 ተፈናቃዮች በ34 መጠለያ ጣቢያዎች እንደሚገኙ የተገለጸ ሲሆን፣ ሌሎች ተፈናቃዮች ደግሞ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች እንደሚገኙ ተጠቁሟል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ግብይቱም የምርትና ምርታማነቱን ዓይነት ርብርብ ይጠይቃል!

ወቅቱ አዝመራ የሚሰበሰብበትና ገበያው መጥገብ የሚጀምርበት ነው።አርሶ አደሩ ውሎዉም አዳሩም አውድማው አካባቢ ነው። በሀገራችን የግብርና ሥራ በዚህ የመኸር ወቅት አዝመራ እየተሰበሰበና እየተወቃ ምርቱ ወደ ጎተራ ይገባል።አርሶ አደሩ ምርቱን ወደ ገበያ የሚያወጣበትም ነው።

ይህ ዘመን ደግሞ በግብርናው ዘርፍ ላይ የተከናወኑ ሰፋፊ ተግባሮችን ተከትሎ ለውጦች እየታየ ያለበት ነው።አርሶ አደሩ በተበጣጠሰ ማሳ ያመርት ከነበረበት ሁኔታ ወደ ኩታገጠም ማሳ በእጅጉ የገባበት፣ የማዳበሪያና ምርጥ ዘር አቅርቦት ላይ በስፋት የተሠራበት ሜካናይዜሽን ትርጉም ባለው መልኩ የታየበት ሆኗል።ግብርና ሲሰጡት ይሰጣል እንደሚባለው ይህን ሁሉ ተከትሎ ምርትና ምርታማነት ላይ ለውጦች ታይተዋል ።

ግብርና የሀገሪቱን የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ ባለፈው በውጭ ንግዱን የመሪነቱን ሚና እየተጫወተ ይገኛል።ባለፈው በጀት ዓመት ከተለያዩ ዘርፎች በወጪ ንግድ ከተገኘው ገቢ ግብርናው ያስገኘው ገቢ የላቀ መሆኑም ይህንኑ ያመለክታል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ መንግሥት በስንዴ ልማት ላይ እያደረገ ያለውን ጥረት ተከትሎ ግብርናው ለሀገሪቱ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ ጨምሯል።በሀገሪቱ ስንዴ ከመኸር ወቅት በተጨማሪ በበጋ መስኖ ከአንዴም ሁለቴ በስፋት እየተመረተ ይገኛል።በመኸር ወቅት የሚገኘው የስንዴ ምርት እየጨመረ ሲሆን፣ በበጋ መስኖ የሚገኘውም ምርትም እየጨመረ መጥቷል። ይህ ሁኔታ ዘርፉ የሀገር ኢኮኖሚን በመደገፍ በኩል ያለው ሚና እየጨመረ መምጣቱን ያመለክታል።

በመኸሩም በመስኖውም ስንዴ ለማምረት እየተደረገ ያለው መጠነ ሰፊ ርብርብ የሀገሪቱን የስንዴ ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር ሀገሪቱ ከውጭ ታስገባ የነበረውን የስንዴ ምርት ለማስቀረትና የውጭ ምንዛሪ ለማዳን እንዲሁም ወደ ጎረቤት ሀገሮች ስንዴን በመላክ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ነው።

በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የሚገኘው ምርት ከዓመት ዓመት እየጨመረ መጥቷል።ባለፈው በጀት ዓመት ከበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ብቻ 26 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ተገኝቷል።በ2014/15 በበጋ መስኖ ደግሞ 52 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማምረት ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል። ይህ ልማት ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ምርታማነቱ እንዲቀጥል ግብርናው ላይ የሚከናወነው ተግባር ዋናው ቢሆንም፣ ከዚህ ባልተናነሰ መልኩ ግብይት ላይ መሥራትም ያስፈልጋል። አርሶ አደሩ ከምርቱ ተገቢውን ገበያ ማግኘት ይኖርበታል፤ የድካሙን ያህል ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩ ምርታማነቱ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ገበያ ማግኘት ይኖርበታል። ይህን ዓይነቱ ገበያ ደግሞ በተለመደው መንገድ ሊፈጸም አይችልም፡፡

እንደሚታወቀው የሀገራችን ግብይት ጤነኛ አይደለም፤ በደላሎች፣ በሕገወጥ ወይም ስግብግብ ነጋዴዎች የተሞላ ነው።ገበያውን ከእነዚህ አካላት መታደግ ያስፈልጋል።ይህ ደግሞ የመንግሥትን፣ በግብይት ላይ ሰፊ ሥራ እያከናወኑ የሚገኙትን የኅብረት ሥራ ማኅበራትን፣ ምርት ገበያንና ሌሎች የግብርናው ዘርፍ አካላትን የተቀናጀ ርብርብ ይፈልጋል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በሀገር ውስጥ ከሚያደርጉት የስንዴ ግብይት በተጨማሪ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ግዥ ለመፈጸም እየሠሩ ናቸው።የኢትዮጵያ ምርት ገበያም እንዲሁ አቋርጦት የነበረውን ስንዴ የማገበያየት ሥራ ይጀምራል።

መንግሥት በመኸር ወቅትና በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ ሊገኝ የሚችለውን ምርት ታሳቢ በማድረግ ሀገሪቱ በዚህ ዓመት ስንዴ ለጎረቤት ሀገሮች እንደምታቀርብ ማስታወቁ ይታወሳል። ይህን ተከትሎም አንዳንድ የአፍሪካ ሀገሮች ፍላጎት ማሳየታቸው ሲገለጽም ነበር። ይህ መንግሥት ባከናወነው ተግባር የተገኘ ጥሩ ምላሽና ነውና በሚገባ ለመጠቀም በግብይት ላይ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል።

የዘንድሮውም ሆነ ቀጣዩ ግብይት ከዚህም በላይ የላቀ ጥረትን ይጠይቃል።በመስኖ ስንዴ እየተመረተ ያለበት ሁኔታ በመኸር ስንዴ በብዛት እየተመረተ ያለበት ሁኔታ ግብይቱም ሰፊ ሥራን እንደሚፈልግ ያመለክታል። የኅብረት ሥራ ማኅበራቱን እና የምርት ገበያውን ተነሳሽነት በሚገባ መጠቀም ያስፈልጋል።

ግብይቱ ላይ መሥራት የሸማቹን ፍላጎት ማሟላት እንዲሁም ለውጭ ገበያ የሚቀርበው ስንዴ በተያዘው እቅድ መሠረት እንዲፈጸም ማስቻል ነው።ማኅበራቱ የሚያነሷቸው የመጋዘን፣ የፋይናንስ አቅርቦትና የመሳሰሉት ችግሮች ከተፈቱ እቅዳቸውን በማሳካት ግብይቱን ማሳለጥ ይቻላል።ለአርሶ አደሩ ከማኅበራቱ በላይ በቅርበት የሚገኝ የለም።ይህን አቅም በሚገባ መጠቀም ይገባል፡፡

ግብይቱ ላይ በትኩረት መሥራት ከጠቅስናቸው ጉዳዮች በላይ የተሻገረ ፋይዳም እንዳለው መገንዘብ ይገባል።በግብርና ሥራ ውስጥ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ አንድ ነገር ነው፤ ብቻውን ግን ብዙ ርቀት አያስጉዝም።ምርቱ ገበያ እንዲያገኝ አበክሮ መሥራትንም ይጠይቃል። የግብርና ምርት ሲትረፈረፍ ዋጋ ወድቆ አርሶ አደሮች ሊጎዱ እንደሚችሉ አስቀድሞ በማሰብ የእነሱንና የሸማቹን ፍላጎትና ተጠቃሚነት ባረጋገጠ መልኩ ግዥዎች እንዲፈጸሙ ማድረግ ያስፈልጋል።

ግብይቱን ከሕገወጦች መታደግም ያስፈልጋል።በዚህ የምርት ወቅት አንዳንድ የእህል አይነቶች ዋጋ እየጨመረ መሆኑን መረጃዎች እያመለከቱ ናቸው። እህል የመደበቅ ነገር እንዳለም እየተጠቆመ ነው።ይህ የሚያመለክተው ሕገወጦች ገበያውን እየተቆጣጠሩት መሆኑን ነው።ስለሆነም ይህ ጉዳይ በጊዜ መፍትሔ ይፈልጋል፡፡

በግብይቱ አርሶ አደሮች በእርግጥም ተጠቅመው ከሆነ እሰየው ነው። የመጣንባቸው መንገዶች ግን ይህን አያመለክቱም። ገበያው በደላሎችና ስግብግብ ነጋዴዎች ቁጥጥር ስር ሲውል ነው የኖረው። ይህ መፍትሔ ይፈልጋል።ለዚህ ደግሞ የኅብረት ስራ ማኅበራት ፍቱን መድኃኒት መሆናቸው እርግጥ ነው።

ኅብረት ሥራ ማኅበራት የአርሶ አደሩም፣ የሸማቹም፣ የመንግሥትም የቅርብ አካላት ናቸው።የማኅበራቱን አቅም በማጠናከር ግብይቱ በእነሱ በኩል እንዲፈጸም ማድረግ ፋይዳው ብዙ ነው።ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ያህል ግብይትም ላይ ማተኮር ወቅቱ የሚጠይቀው ዐብይ ተግባር መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

# የመላውን ሕዝብ ተሳትፎ የሚጠይቀው የፀረ-ሙስና ትግል

**ክብረአብ በላቸው**

ሀገራት በተለያዩ ጊዜያት በእጅጉ ከሚፈተኑባቸው ችግሮች መካከል ሙስና ወይም ሌብነት አንዱና ዋነኛው ነው። በመላው ዓለም ማለት በሚቻል ደረጃ መጠኑ ቢለያይም ችግሩ በእጅጉ ተንሰራፍቶ ይገኛል ፤ለሀገራትንም የዕድገታቸው ነቀርሳ ሆኖ ዋጋ እያስከፈላቸው ይገኛል ፡፡

ችግሩ በተለይም ባላደጉ እና እያደጉ ባሉ ሀገራት በስፋት የሚስተዋል ሲሆን የሀገራቱ ሕዝቦችን የመልማት ተስፋ ከማቀጨጭ አንስቶ በድህነታቸው ላይ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖባቸዋል ።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በዓለም በየዓመቱ በሙስና እስከ አራት ትርሊዮን ዶላር ይመዘበራል።አፍሪካም በየዓመቱ 50 ቢሊዮን ዶላር በሙስና ምክንያት እንደምታጣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እኤአ በ2021 ያስጠናው ጥናት ያመለክታል።

ሀገራችን ቢሆን የችግሩ ሰለባ መሆን ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል። የተለያዩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በኢትዮጵያ በተለይም በመሬት ነክና አገልግሎት ዘርፎች ሙስና ጎልቶ ይስተዋላል። እንደ ግሎበል ፋይናንሺያል ኢንተግሬት ጥናት ከሆነ ሀገሪቱ እኤአ ከ2000 እስከ 2011 ብቻ ከ12 ቢሊዮን ዶላር በላይ በሙስና አጥታለች።

የሀገራችን ባህላዊ እና መንፈሳዊ እሴቶች ሌብነትን የሚጠየፉ ፤ እንደ ነውር የሚቆጥሩ ቢሆንም ችግሩ ግን ስር ሰድዶ የሀገር ደህንነት ስጋት የሚሆንበት ደረጃ ስለመድረሱን አምርረው የሚናገሩ እየበዙ ነው ።

‹‹ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል፡፡›› እና የመሳሰሉት ሙስናን/ሌብነትን የሚያበረታቱ፤ ለሙስና አስተሳሰብ መሠረት የሆኑ አባባሎች በተለይም በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ችግሩ ከመጠን በላይ እንዲንሰራፋ የራሱን አስተዋጽዖ አበርክቷል።

ችግሩ ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ አብዛኛውን የሀገሪቱን ዜጋ እያስመረረ ያለ፤አገልግሎቶችን በእጅ መንሻ ካልሆነ በስተቀር ማግኘት እስከማይቻልበት ደረጃ እንዲደርስ ያደረሰ ነው ። ይህ እጅግ አስፋሪ የሆነ ትውልድ አጥፊ ድርጊት በየጊዜው መልኩን እየቀያየረና እየረቀቀ ሄዷል።

በቅርቡም መንግሥት ሙስና/ሌብነት የብሔራዊ

**አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የማይጠበቁና ድንገታዊ ግጭቶችን በመፍጠር የመንግሥትን ትኩረት ከሙስና ትግሉ ይልቅ ግጭቶችን በመፍታት እንዲወጠር የማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ይህም በሌብነት የተገኘ ሀብትን በማሸሽ ከሕግ ተጠያቂነት ለማምለጥ እየተደረገ ያለ እንቅስቃሴ አካል እንደሆነ ይታመናል፡፡**

ደህንነት ስጋት ነው ብሎ በመለየት ይህን አደባባይ የሞላ ወንጀል ለመከላከል ብሔራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴ አቋቁሞ ወደ ሥራ ገብቷል። የፀረ ሙስና ትግሉ ውጤታማ እንዲሆንም ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርቧል፡፡

ችግሩ በእርግማን ብቻ ሊጠፋ እንደማይችል በመገንዘብ መላው ሕዝብ የፀረ ሙስና ትግሉ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሊሆን እንደሚገባ ፤ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነትና ዝግጁነት እንደሚያስፈልግም አመልክቷል።

ከጸረ-ሙስና ዘመቻው ማግስትም መንግሥት ይህን የብሔራዊ የደህንነት አደጋ ለመከላከል በሌብነት የተጠረጠሩ ከከፍተኛ የመንግሥት ባስልጣናት እስከ ታች የሥራ ኃላፊዎች ድረስ በቁጥጥር ስር በማዋል ምርመራ እያደረገ ስለመሆኑ እያየንም፤ እየሰማንም እንገኛለን፡፡

“ግርግር ለሌባ ያመቻል”እንዲሉ፤ ይህንኑ የፀረ ሙስና ትግል ዘመቻ ለመግታት በሚመስል መልኩ በተለያዩ የሀገሪቱ ስፍራዎች የፀጥታ ችግር በመፍጠር የመንግሥትን ትኩረት ለማስቀየር መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ እያስተዋልን ነው፡፡

አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የማይጠበቁና ድንገታዊ ግጭቶችን በመፍጠር የመንግሥትን ትኩረት ከሙስና ትግሉ ይልቅ ግጭቶችን በመፍታት እንዲወጠር የማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው።ይህም በሌብነት የተገኘ ሀብትን በማሸሽ ከሕግ ተጠያቂነት ለማምለጥ እየተደረገ ያለ እንቅስቃሴ አካል እንደሆነ ይታመናል፡፡

በሌላ በኩል በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ሲካሄድ የነበረው ጦርነት በሰላም ስምምነት መጠናቀቁ ደስታ ያልፈጠረባቸው ታሪካዊ ጠላቶቻችን ጨምሮ ሀገሪቱ ከግጭትና ጦርነት ተላቃ ፊቷን ወደ ልማት በማዞር ስኬታማ እንዳትሆን የሚሹ ኃይላት በተመሳሳይ መንገድ ስለጥፋት ሰልፍ የማሳመራቸው እውነታ የሚጠበቅ ነው።

ሀገሪቱ ከለውጡ ማግስት ያለመችው ብልጽግና እውን እንዳይሆን፤ከዚህ ይልቅ በተራዘመ ጦርነትና ግጭት እንዲሁም በሙስናና ሌብነት የተራቆተችና የደቀቀ ኢኮኖሚ ያላት ሀገር እንድትሆን ረጅም መንገድ ከመሄድ አይመለሱም ።

ይህንንም ምኞታቸውን እውን ለማድረግ የጥፋት ኃይሎችን ከመፍጠርና ከመደገፍ አይመለሱም ፤ለዚህም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በምዕራብ ኦሮሚያ በተለያዩ የወለጋ ዞኖች በታጣቂ ኃይሎች የሚፈፀሙ ጥቃቶች ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ይህ አጠቃላይ የሆነውን የመንግሥት የልማትና ይህን ተከትሎ የመጣውን የጸረ-ሙስና ትግል ለማሰናከል እየተደረገ ያለ የሞት ሽረት ትግል ለመቀልበስ የመላው ሕዝባችን የነቃ ተሳትፎ ወሳኝ ነው ፡፡

ሕዝቡ ከእያንዳንዱ የሁከትና የብጥብጥ አጀንዳ በስተጀርባ ያለውን እውነታ በሚገባ ተረድቶ ብዙ ዋጋ የከፈለለትን ለውጥ በማስቀጠል የበለጸገች ሀገር ለመፍጠር የተጀመረው ትግል ስኬታማ እንዲሆን ከፍ ባለ ቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል ።

## ፍረዱኝ

# ‹‹ የስኳር አቅርቦት ችግር ሙሉ ስሙሉ ባይፈታም ማስታገስ ግን ይቻላል››

አቶ ዘመድኩን ተክሌ
የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ የኮርፖሬት ጉዳዮች ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**ስኳር በአሁኑ ወቅት አንገብጋቢ ከሚባልበት የሰው ልጅ ፍላጎት ላይ ደርሷል፡፡የስኳር አቅርቦትና ፍላጎቱ ባለመጣጣሙም እጥረቱ ጎልቶ ዋጋውም አሻቅቦ ይገኛል። ‹‹በመጋዘን የስኳር ክምችት የለም›› የሚባልበት ደረጃም ተደርሷል። ለመሆኑ ይህ ችግር እንዴት ተከሰተ? አሁናዊ ችግሮችና ቀጣይ የተስፋ ጭላንጭሎች ምንድን ናቸው? ስንል የዝግጅት ክፍላችን ከኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ የኮርፖሬት ጉዳዮች ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ከአቶ ዘመድኩን ተክሌ ጋር ቆይታ አድርጓል-መልካም ንባብ፡፡**



**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ የቀድሞ ስሙ €€ስኳር ኮርፖሬሽን‹‹ ነው።የተቀየረው ስሙ ወይስ ግብሩና ተልዕኮው ጭምር ነው?**

**አቶ ዘመድኩን፡-** ከስያሜ ለውጡ ጋር የሚነገር ምንም ነገር የለውም።ዱሮ ስኳር ኮርፖሬሽን በሚባል ጊዜ ስኳር ላይ የሚሰሩትን ፋብሪካዎችና ፕሮጀክቶችን በሙሉ ይዞ ይሄድ ነበር።ስኳር ኮርፖሬሽን ቢባል ያን ያህል ለውጥ የሚያመጣ አልነበረም። ግን ስም አንዳንዴ ጊዜ የሚፈለገውን ስኬት ያላመጣ ከሆነ አብሮ መለወጥ ጥሩ ነው ስለሚባልና በዚህ ዕምነት ነው። ስኳር ኮርፖሬሽን በጣም ትልልቅ ሥራዎችን ሰርቷል፤ ግን የሚፈለገውን ያህል ውጤት የተገኘበት አይደለም። ውጤት የተገኘበት ባለመሆኑም እሱንም ጭምር ለመቀየር ነው።ተቋማት ተልዕኮ ሲለውጡ ስማቸውንም አብረው ስለሚለውጡ ከዚህ ጋር አያይዞ ማየት ጥሩ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ብዙ ህፀፆች የነበሩበት ተቋም በመሆኑ ሪፎርም ማድረጉ ይታወቃል።አሁን ምን ለውጥ ተገኘ?**

**አቶ ዘመድኩን፡-** ስኳር ኮርፖሬሽን በ2003 ዓ.ም ሲቋቋም የሀገራችን የመጀመሪው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በሚል ሁላችንም እንደምናስታውሰው በጣም ሰፋፊ ስራዎች ታቅደው የተጀመሩበት ጊዜ ነው።በአንድ በኩል ፈጥኖ ለማደግ ካለ ፍላጎት የመነጨ በጎ አስተሳሳብ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።በሌላ በኩል ደግሞ አቅምን በማገናዘብ በኩል የተሟላ ጥናት አድርጎ የሥራዎችን ባህሪ በመለየት ወደ ሥራ በመግባት ረገድ ጉድለቶች ነበሩት።ከዚያ ጋር ተያይዞ ኢንዱስትሪው ላይ ከበድ ያለ ጉዳት ያደረሱ ውሳኔዎችና ጅምር ስራዎች ተሰርተዋል።ምንም እንኳን በአንድ ጊዜ ሰፋ ያሉ ስራዎችን በመስራትና በማቀድ ለውጥ ለማምጣት የተገኙ ጥሩ ነገሮችና ብዙ ልንሰራ እንደምንችል የታዩባቸው ውጤቶች ያሉ ቢሆንም፤ የስኳር ፋብሪካ በባህሪው እና ስራው በጣም ውስብስብ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ዘለግ ያለ ጥናት የሚፈልግ ነው፡፡

ትልቅ ኢንቨስትመንትና የተሟላ የሠው ኃይል የሚፈልግ ቢሆንም እነዚህ ባልተሟሉበት ሁኔታ በመላ ሀገሪቱ በሚባል ደረጃ በጥድፊያ በጣም ብዙ ሥራዎች ተጀምረዋል፤ ይህ እንዳሰብነው ውጤታማ ሊያደርገን አልቻለም።የሥራውን አዋጭነት፣ ስፋት፣ ለሥራው የሚስፈልገውን ግብዓት፣ ፋይናንስ፣ የሰው ኃይልና የመሳሰሉትን በደንብ አላየንም፤ በደንብ አላዘጋጀንም።በፍላጎትና በጥድፊያ የተገባበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በሀገሪቱ ላይ በጣም ትልቅ ኪሳራ አድርሷል፡፡

የስኳር ልማት የተጀመረው በመላ ሀገሪቱ በሚባል ደረጃ ነው። በአንድ በኩል የልማት ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ የሚል እሳቤም ከበስተጓላው ነበረው።የልማት ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ ቢሆን በራሱ አውድ በደንብ መታየት የነበረበት ነገር ነው።ስኳር አዋጭ በሆነ ቦታ ስኳር፤ ሌላ ነገር በሚያወጣበት ቦታ ደግሞ ሌላ ነገር እያደረጉ ነው አካባቢን የበለጠ ውጤታማ የሚያደርገው። ይሁንና የልማት ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ ስኳር ያን ያህል አዋጭ ላይሆን ይችላል። መሠረታዊ የሚባሉት አየሩ፤ ውሃው፣ አፈሩና የመሳሰሉትን ታይተዋል።ነገር ግን ከዚህም በላይ ስኳር ልማት ላይ በደንብ መታየት የነበረባቸው ነገሮች አልታዩም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በደንብ መታየት የነበረባቸው ያልታዩት ምንድን ናቸው? አሁንስ እልባት አግኝተዋል?**

**አቶ ዘመድኩን፡-** ዋና ዋና ችግሮቹ አንደኛው የአዋጭነት ጥናት ነው። ስኳርን ለሚያክል ትልቅ ፕሮጀክት ቀርቶ ለትንንሽ ፕሮጀክቶችም እንደቢዝነስ ሲታዩ አዋጭነታቸው መታየት አለበት።የሚሠራበት ፋይናንስ፣ የሚገኘው ምርት፣ የሚጠናቀቅበት ጊዜ እንዲሁም ገንዘብ መመለስ የሚጀምረው መቼ ነው የሚለውና የመሳሰሉት በደንብ መታየት ነበረባቸው። እዚህ ላይ የአዋጭነት ጥናት በደንብ አልታየም።በጥቅሉ ኢትዮጵያ ለአገዳ ልማት ሊውል የሚችል ተስማሚ አፈር፣ ውሃና አየር አላት ከሚል ጥቅል መነሻ የተነሳ ነው።ይህ ጥቅል መነሻ ጥሩ ቢሆንም በጣም በዝርዝር ኢኮኖሚያዊ ገጽታው በሚገባ መፈተሽ ይገባል።ስለዚህ ጥልቅ ጥናት አለመደረጉ አንደኛው ችግር ነው፡፡

ሁለተኛው የስኳር ልማት በጣም ሰፊ ነው።እንደ እኛ ሀገር ስኳር ኢንዱስትሪን ሙሉ አሟልቶ አንድ ላይ የሚሠራ ሀገር የለም።በሌላ ሀገር ብንሄድ ‹‹ሚለርስ›› ይባላሉ፤ ፋብሪካውን ነው የሚይዙት።መስኖ በሌላ አካል ይሰራል።ውሃ አቅራቢ ሌላ ሊሆን ይችላል። በእኛ ሀገር መሰረተ ልማት፣ መስኖ፣ ፋብሪካ መገንባትና የመሳሰሉትን ትልልቅ ሥራዎችን በሙሉ በአንድ ተቋም ነው እንዲሠራ የተደረገው።እነዚህ ዝግጅት ይፈልጉ ነበር። ሌላው ቀርቶ በቂ ፋይናንስ እና ግምት አልተወሰደም ነበር።መደጋገም አሰልቺ ይሆናል እንጂ፤ የሀገር ውስጥን አቅም ማሳደግ በሚል እሳቤ ስራውን ለመሥራት የሄድንበት መንገድም ችግር ነበረበት።ለምሳሌ ‹‹ሜቴክ›› የሀገር ውስጥ ኮንትራክተር ሆኖ ብዙ ሥራዎችን በአንድ ጊዜ ጠቅልሎ የያዘበት ሁኔታ መስሪያ ቤቱንም ሀገሪቱንም ጎድቷል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁንስ አጠቃላይ ኪሳራው ታይቷል?**

**አቶ ዘመድኩን፡-** የሆነው ነገር ተራ የባለሙያ ስህተት አይደለም። በባለሙያ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካሊ የተመራ ሥራ ነው። በመንግስትና በፖሊሲ አቅጣጫ የተመራ ሥራ ነው። ከዚህ አኳያ ያለፍንበት ሁኔታ መልሰን ብንደጋግመው ያሰለቻል፡፡

ልማቶች ይመሩበት የነበረው መንገድ ሙያውን በጣም የጨቆነ፤ የሙያ ሥራ ብዙ የማይሰማበት የፖሊሲ አቅጣጫው ገፍቶ የሚሄድበት ሁኔታ ነበር። ይህ አይሆንም ሲባል የሚሰማ አልነበረም፤ እንዲያውም እንደ አደናቃፊ የሚታይበት ሁኔታ ነበር።ለምሳሌ የስኳር ፋብሪካ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ውስጥ አይጠናቀቅም።ግን በዚህ ላይ የሚሰጥ ሙያዊ አስተያየት እንደ አደናቃፊ ይታይ ነበር።እነዚህን የመሳሰሉት ከባድ ነገሮች ነበሩ።እንደ ሀገር፣ ዜጋ፣ ተቋም ከ2007 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ነገሮች አለመሳካታቸው ሲታይ በተወሰነ ደረጃ ይህ ነገር አይሆንም መስተካከል አለበት በሚል በመስሪያቤታችን በኩልም ግፊት መደረግ ተጀመረ።

ሜቴክ ይመራና ይሰራ የነበረውን ሁኔታ እናውቀዋለን። በ2008 ዓ.ም ደግሞ ይህ ነገር ገፍቶ ቆመ። ለተሰራው የሥራ ክፍያዎችን መፈፀም የማቆም እና የመሳሰሉት ነገሮች ውስጥ መስሪያቤታችን ገባ።ስለሆነም የመጀመሪው ማስተካከያ እርምጃዎች ችግሩ ያስከተለው ጉዳት በጣም ሰፊ እንደሆነና በአጭር ጊዜ መመለስ እንደማይቻል በዝርዝር ታይቶ፤ ወደፊት በሚስተካከልበት ሁኔታ ነው ወደ ስራ የተገባው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በስኳር ልማት ስኬታማነት ጎን ለጎን የመንገድ፣ ትምህርት ቤት፣ የጤና ተቋማት መስፋፋት ያመጣል በሚል ሕብረሰቡ ተስፋ ነበረው።ይህ ባለመሆኑ የደረሰው የሥነ-ልቦና ጫና፣ ፖለቲካዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ኪሣራ ጥርት ብሎ ይታወቃል?**

**አቶ ዘመድኩን፡-** በቢሊዮን የሚቆጠር ኪሳራ ደርሷል። አሁን ዓመታትን አስቆጥረን ጉዳቱን ለመርሳት እየሞከርን ነው። ሕብረተሰቡም ዘንድ የተፈጠረው ሥነ ልቦናዊ ጉዳት ቀላል አይደለም።የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶችን በወቅቱ ይጠናቀቃሉ ወይ ብሎ ያለማመን ችግር አስከትሏል፡፡

መሬቱን የለቀቀ፣ ሥራ ዕድል ለማግኘት ያሰበና ይህ ሳይሆን ሲቀር የሚፈጠረውን ችግር በቀላሉ የሚገመት አይደለም።ከዚህም በላይ እንደ ሀገር ያጣነው ሃብት ቀላል አይደለም። ሠርተን ልናመጣ የምንችለው ሃብት መቅረቱ ብቻ ሳይሆን፤ ያባከንነው ሃብት በጣም ብዙ ነው። ፋብሪካ ይደርሳል ብለን አገዳ ተክለን ቆርጠን አስወግደናል።ፋብሪካ በደረሰበት አገዳ መድረስ አቅቶት፤ አገዳ በደረሰበት ደግሞ ፋብሪካ አልደርስ ብሏል። ምክንያቱ ደግሞ በተናጠል ሁሉም እየሮጠ፣ ብክነት እያስከተለ የሄደበት ሁኔታ አለ።ይህ ስኳር ላይ ብቻ ሳይሆን ብዙ ቦታ ላይ አጋጥሟል።በመሆኑም በኢኮኖሚው፤ በማህበራዊ እና በመሳሰሉት ነገር የደረሰው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም።እነዚህን ነገሮች ደምረን ስንመለከታቸው የማስተካከል ሥራዎች በምን ላይ ያተኮሩ ናቸው ወደሚለው ይወስደናል፡፡

አዲስ ዘመን፡- በአሁናዊ የማስተካከያ እርምጃዎች ምን ያህል ውጤታማ ሆናችሁ?

አቶ ዘመድኩን፡- በተለይ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በስፋት ሥንሠራ የነበረውና በኋላም ተጠናክረው የቀጠሉ አሉ። አንደኛው ፕሮጀክቶችን በህግና ፕሮጀክቶች በሚመሩበት አቅጣጫ መምራት የሚል ነው።በጣም ትልቁና እዚህ ቤት ያስፈልግ የነበረው አካል ፕሮጀክቶች በሚመሩበት ህጋዊ አግባብ መምራት ነው።መጀመሪያ ለማተስካከል የሞከርነው ይህንን ነው።ከዚህ በፊት ላልተሰራ ሥራ ክፍያ ይፈፀም ነበር።አሁን ኮንትራክተር፤ ደንበኛ፣ አሰሪ እና አማካሪ ሦስቱ ተቀናጅተው ነው ሥራ የሚሰሩት።ቀደም ብሎ ግን ይህ አልነበረም።ስለዚህ የኮንትራት አስተዳደር ህግን መተግበር የመጀመሪ ሥራችን ነበር፡፡

ሁለተኛው ስራችን የነበረው ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ኢንዱስትሪን በጣም የጎዳው ባለሙያዎች ከተቋሙ ተገፍተው እንዲወጡ ተደርገው ነበር።ሙያውን የማያውቁ ሰዎች ይመሩት ነበር።ይህን ወደባለሙዎች የመመለስ ሥራ ተከናውኗል።ሦስተኛው ፋብሪካ እና የአገዳ ልማትን የማጣጣም ሲሆን፤ በዚህ ላይ ትልቅ ጉድለት ነበር።ፋብሪካ በትክክል የሚደርስበት ጊዜ ተረድቶ፤ በዘርፉ ላይ እውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች ወደ ሥራ አስገብቶ አገዳ ልማቱንም አብሮ የማስኬድ ሙከራ የተደረገበት የለውጥ ስራ ነው፡፡

አራተኛው ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ወደኋላ የቀሩ ፋብሪካዎችን ማጠናቀቅ ነው፤ በዚህም ትልቅ ለውጥ ተገኝቶበታል።ለምሳሌ በለስ ስኳር ፋብሪካ ለብዙ ዓመታት መቆሙ ብቻ ሳይሆን መጨረሻው ምን ሊሆን ይችላል የሚል ግምት ነበር። በለስ በጀቱ የተያዘው ሜቴክ ሲገነባ በነበረ ጊዜ ነው። በጀቱ በሙሉ ግን ሥራው ሳይሠራ ተከፍሎ አልቋል። በዚህም የተነሳ በምን በጀት ማን ሰርቶ ይጨርሰዋል፤ እንዴትስ ይሰራል በሚል ትልቅ ችግር ነበር። ኦሞ አካባቢም ተጀምረው የነበሩና ያላለቁ ፋብሪካዎችን በተለየ ውሳኔና የመንግስት የቅርብ ክትትል ተጠናቀው ሥራ እንዲጀምሩ የተደረገበት ሁኔታ በጣም በትልቁና በለውጡ ሂደት ከተሳኩ ነገሮች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የተቋሙ የፋይናንስ አሰራርም የራሱ ችግር ነበረበት። ለብዙ ዓመታት ሂሳብ እንደ ተቋም ተጠቃሎ አልተዘጋም። እዚህ ቤት የሚንቀሳቀሰው ገንዘብ በጣም ትልቅ ነው።እንደ ተቋም በየፕሮጀክቶቹና ፋብሪካዎቹ የገባው ገንዘብ ተጠቃሎ ከመዝጋት አኳያ ችግር ነበረበት። ይህም የተቋሙን የሃብት ቁመና ለማወቅ አስቸጋሪ አድርጎት ነበር። በመሆኑም ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የመዝጋትና የማስተካከል ሥራ ተከናውኗል። ብክነት ለመቀነስም ብዙ ሥራ ተሰርቷል። ቀደም ሲል ሃብት በቁጠባ የመጠቀም ባህል አልነበረም።ፋብሪካ እና አገዳ ልማት አለመጣጣምና ብክነት ነበረበት። በተጨማሪም ስኳር መመረቱን እንጂ በምን ያክል ወጪ ቆጣቢ ነበር የሚለው ማወቅ አስቸጋሪ ነበር፡፡

ኢንዱስትሪ ደግሞ በቁጠባ ካልተመረ አትራፊ መሆን አይቻልም።በመሆኑም ይህን አሰራር ለማስተካከል ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል።በመሆኑም ቀደም ሲል ያልነበረና አሁን እየተተገበረ ያለ ነገር ቢኖር ለእያንዳንዱ ፋብሪካ የማምረቻ ወጪ የሚል ተሰልቶ እየተሰራበት ነው። በመሆኑም ይህ ውጤታማ እያደረገን ነው። ውጤታማ ያልሆኑ ፋብሪካዎችንና

# ፍረዱኝ

ሥራዎችን የማቆም ስራም ተተግብሯል።ለምሳሌ ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በአካባቢው አጋጥሞ ከነበረው ድርቅ አኳያ ለምቶ የነበረው 20ሺ ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ልማት ሙሉ ለሙሉ ወድሟል።ይህም በመሆኑ ስራው ለማስቀጠል አልተቻለም፡፡

ሸንኮራ አገዳ ልማት ሰፊ ጊዜና ገንዘብ ይጠይቃል። ሙሉ ለሙሉ በእንስሳት ከመውደሙና ከጸጥታው ጋር ተያይዞ ስኳር ማምረት ስላልተቻለ ብክነት ማስቀረትና ነገሮች በአስተማማኝ ደረጃ እስኪረጋጉ ድረስ እዚያ አካባቢ ያለው ሥራ ሊያሰራ የሚችል የሰው ኃይልና ወጪ በመመደብ ወጪ ከመቀነስ አኳያ ተሰርቷል። ፕሮጀክቶችን ማጣመርና አንድ ላይ እንዲሰሩ የማድረግም ስራ ተከናውኗል። ለምሳሌ ኦሞ አካባቢ ኦሞ አንድ፤ ሦስት እና አምስት በአንድ ማኔጅመንት እየተመሩ ቆይተው በኋላ ሲሰፉና ሲያድጉ በየራሳቸው መቆም ሲያስፈልግ በዚያው አቅጣጫ የሚመሩ ይሆናል፡፡

ሌላው ትልቅ እርምጃ የሚባለው አምስት ፋብሪካዎች ራሳቸውን ችለው እንዲዋቀሩ የተደረገበት ነው። መሰረታዊ ነገር የመንግስት ፍላጎትም ተቋማችንም የሚያምንበት ነገር ነው። የፋብሪካዎቹ ታሪክ በሚታይበት ጊዜ ከሞላ ጎደል ውጤታማ ሆነው የነበሩት ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድሩ በነበረበት ወቅት ነው። ስለዚህ ከስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ ስር ከሚሆኑ ይልቅ በራሳቸው ቦርድ እየተመሩ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲመሩ መጋቢት 2014 ዓ.ም ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን ከአምስቱ ፋብሪካዎች ከሰም እና በለስ ከአዳዲሶቹ ሲሆኑ፤ ወንጂ፣ መተሐራ እና ፊንጫ ስኳር ፋብሪካዎች ደግሞ ከነባሮቹ ናቸው። ይህም የለውጡ ትልቅ ማሳያ ነው። ይህ መደረጉ የስኳር ኮርፖሬሽን የነበረውን ተልዕኮ ለመቀነስ፤ ችግሮቹን በየፈርጁ ለማስተካከል ይረዳል። የተዋቀረው ቦርድም በፖለቲካ እና ሙሉ ተሳትፎ ውሳኔ ለመስጠት ዕድል የሚሰጥ ነው። ይህም ፋብሪካዎቹ ወደቀድሞ ዝናቸው ለመመለስ ያግዛል ተብሎ ይገመታል።እነዚህ ሪፎርሙ ከወሰዳቸው እርምጃዎችና ትልቅ ውጤት ያመጣሉ ብሎ ከሚጠበቅባቸው የሚጠቀሱም ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ፋብሪካዎቹ ማምረት ከማቆም በዘለለ ለስርቆት እየተጋለጡ ነው።ስመሆኑ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙት ፋብሪካዎች የጥበቃ ሁኔታ ምን ይመስላል፤ ቅድሚያ ትኩረትስ የሚሰጠው ለስ?**

**አቶ ዘመድኩን፡-** እውነት ለመናገር ሁሉም ፋብሪካዎች ትኩረት ይፈልጋሉ።የስኳር ፋብሪካ ኢንዱስትሪ በአንድ ጊዜ አይጎዳም፤ ከተጎዳም በአንድ ጊዜ አይመለስም።ለምሳሌ ወንጂ መተሐራና የመሳሰሉት ፋብሪካዎች የተጀመሩት በኔዘርላንድ ባለሃብቶች ነው።በዳበረ የአሰራር ስርዓትና በሂደት ነው የተጀመሩት።አንዱ ከተሰራ በኋላ ሌላው ሲቀጥልና ሲገነባ ነበር።አሁን እንደተጀመረው በአንድ ጊዜ በርከት ያሉት አልተጀመሩም።በዚህ የአሰራር መርህ ፋብሪካዎች በሂደት እየተጎዱ መጡ።በተለይ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ፋብሪካዎቹና ፕሮጀክቶቹ እየተጎዱ መጡ።

የስኳር ፋብሪካዎች ትልቁ በሽታ የሚጀምረው በ2003 ዓ.ም ነው። ፋብሪካዎች ከሚገኙት ገቢ የአገዳ ልማታቸውን እያሳደጉና ማሽኖቻቸውን እየተኩ እንዳይሄዱና ለፕሮጀክት ብቻ ፋብሪካዎቹ ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት አግባብ ፈርሶ ስኳር ኮርፖሬሽን ስር እንዲገቡ በመደረጋቸው ችግር ውስጥ ገብተዋል። ይሄ በሽታ የዓመታት ችግር አስቀመጠ። ሆኖም አሁን ከችግር ሊወጡ እየታተሩ ነው። ከችግሩ እንዲወጡ በራሳቸው ቦርድ ብዙ ተግባራትን እያከናወኑ ነው።ሆኖም ግን ሁሉም ፋብሪካዎች ትኩረት ይፈልጋሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሁሉም ፋብሪካዎች ትኩረት ሲፈልጉ ይችሳሉ። ግን ተንዳሆና የመሳሰሉት ለሥርቆትም ጭምር ተጋልጠዋል።አንዳንድ ፋብሪካዎች ደግሞ ውጭ ሀገር ያረጁና ተነቅለው መጥተው የተተከሉ በመሆናቸው ወትሮም ሥራ አይሰሩም ይባላል።ለፀጥታ ችግርም የተጋለጡ አሉ።ከዚህ አኳያ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የሉም?**

**አቶ ዘመድኩን፡-** አንዳንዱ ዝም ብሎ የሚወራ ነገር ሊኖረው ይችላል። አንዳንዱ የተወሰነ እውነት ሊኖረው ይችላል። ፋብሪካዎቹን በተመለከተ የተሠራበት ነው የሚለው በእኛ ምርመራ የተረጋገጠ ነገር የለንም።የሰራ ማሽን ያስታውቃል፤ ውል አለው፤ ዕቃዎቹ ተጭነው ሲመጡ ወደብ ላይ ሄዶ የሚያረጋግጥ አካል አለ።ወንጂ እኮ ሲቋቋም 30 እና 40 ዓመት የሠራ ፋብሪካ ነው የተተከለው።ዋናው ችግር እሱ አይደለም።አንዱ ሌላው መክሰስ ጥቅም የለውም እንጂ ፋብሪካውን ያመጣው ሌላ አካል ነው።

ተንዳሆ ላይ ውድመት አጋጥሞናል።ማሕበረሰቡ ልማቱን አምኖበት አይደለም የገባው።ሌላው ቀርቶ የአስተዳደር አካሉ ባላመነበት ሁኔታ ገፍቶ ነው የገባው።መንግስት ሲወስን ለጅቡቲ ወደብ ያለውን ቅርበት በማየት ነው።የአየር ንብረቱንም በማየት ሊሆን ይችላል።በተጨማሪም አለግባብ የመጠቀም ፍላጎት በየአካባቢው አለ።በዚህም የተነሳ ፋብሪካው ስኬታማ አልሆነም።በመጨረሻ ደግሞ የአገዳ ልማቱ ሙሉ ለሙሉ በእንስሳት ወድሟል፤ ከውድመቱም በኋላ የንብረት ስርቆት በስፋት ያጋጥማል፡፡

በወሬ ደረጃ የምንሰማው የማይገመት አካል ጭምር እንደሚሳተፍበት ነው።በእኛ በኩል ለማስጠበቅ እንጥራለን፤ ግን ዝርፊያው ከእኛ አቅም በላይ ነው።በሲቪል ለማስጠበቅ ሞክረናል፤ ፌደራል ፖሊስም ለማስገባት ሞክረናል።የሚደርሰው ጉዳት ግን እነዚህ አካላት አቅም በላይ ነው።በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ባጋጠመን የፀጥታ ችግር ነገሩ እንዲባባስና ተጠያቂነት እንዳይሰፍን ዕድል ከፍቷል።እኛም በተደጋጋሚ በደብዳቤ ጠይቀናል። መሰል ችግሮችን ለማስታገስ ትንሽ ጊዜ ይወስዳል፡፡

በእኛ በኩል እስከቻልነው ድረስ ጠቃሚ ንብረቶችን ወደ ሌላ ቦታ ማንቀሳቀስና ጥቅም ላይ ማዋል በሚቻልበት ላይ እየሠራን ነው፡፡ይህም ቢሆን ቀላል አይደለም፤ የማህበረሰብ ንብረት ነው በሚል ጫናው የከፋ ነው። ነገር ግን እስከቻልነው ድረስ ንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ እያደረግን ነው።ነገር ግን ተንዳሆ ፋብሪካ ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ ንብረት እየተዘረፈ ነው። ሌሎቹ ዘንድም ችግር ቢኖርም፤ እንደ ተንዳሆ የለየለትና ለመቆጣጠር ያስቸገረን አላጋጠመንም።በመሆኑም የተንዳሆን በተለየ ሁኔታ መያዝ ተገቢ ነው።

ከጸጥታና ጥበቃ ጋር ተያይዞ ያለው በደንብ ይታወቃል።አቅም በፈቀደ መጠን ጥበቃ ይደረጋል።ግን አብዛኞቹ ቦታዎች ከሲቪል መስሪያ ቤት አቅም በላይ ነው።ለምሳሌ አርጆ ደዴሳ፣ ፊንጫ ትንሽ አስቸጋሪ ነው፤ ሥራ ይፈልጋል። ሌላው ቀርቶ ቅርቡ መተሐራ እንኳን አስቸጋሪ በመሆኑ የመንግስትን ሥራ ይፈልጋል። ሪፖርት እናደርጋለን፤ መንግስት ወደ ሰሜኑ ትኩረት ስላደረገ ወጣ ገባ ያለ ነገር ነው ያለው።አሁን የሰሜኑ የራሱን መልክ እየያዘ ስለሆነ ይሻሻል የሚል እምነት አለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡-የስኳር አቅርቦት ቀጣይ ተስፋ ምን ሲሆን ይችሳል?**

**አቶ ዘመድኩን፡-** እውነቱን ለመናገር በየትኛው ጊዜም ቢሆን ስኳር የፍላጎቱን ያክል ቀርቦ አያውቅም። መሠረታዊ የሆኑ ፍላጎቱን በመለሰ መልኩ ሲመራ ነበር።ግን ከገጠር እስከ ከተማ ሙሉ ለሙሉ መልሶ አያውቅም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ዘንድሮ ትልቅ ችግር አጋጥሞናል። ዘንድሮና አምና በክረምቱ በተለየ ሁኔታ የስኳር እጥረትና ችግር አጋጥሞናል፡፡

የስኳር ኢንዱስትሪ በአንድ ጊዜ አልሞተም፤ ልክ እንደ ካንሠር በሽተኛ በሂደት ነው የተጎዳው።በሂደት የማምረት አቅማቸው እየቀነሰ ባለፈው ዓመት አስደንጋጭ ደረጃ ደረሱ። ሦስት ሚሊዮን ኩንታል ስኳር ስናመርት በጣም ዝቅተኛ ነው ብለን ነው የምንሳቀቅ የነበረው። ባለፈው ዓመት ግን ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ስኳር ማምረት አልቻልንም፡፡

ትልቁን ምርት ያመርት የነበረው ፊንጫ ከፀጥታ ችግር የተነሳ ማምረት አልቻለም።መተሐራ ላይ 1000 ሄክታር መሬት የሸንኮራ አገዳ ልማት በጎርፍ ጠፍቷል፤ በዚህ ላይ የፀጥታ ችግር ተጨመረበት። ወንጂ ፋብሪካም በተመሳሳይ ሁኔታ የአገዳ ችግር አጋጠመው። አንዳንዱ ችግር ያልተጠበቀ ነው።ከሰም በተመሣሣይ ሁኔታ አሚባራ የሚባል የግል ባለሃብት ነበር። እዚህ ላይ ከአዋሽ ወንዝ ሙላት ጋር በተያያዘ የጎርፍ አደጋ አጋጠመው። ስለዚህ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ተደራርበው ባላፈው ዓመት ችግሩን አባብሰውታል፡፡

የስኳር ፍላጎትን ለማሟላት ጥረት የምናደርገው ሀገር ውስጥ የሚመረተውና ጉድለቱን ከውጭ እያመጣን ነው። ባለፈው ዓመት የነበረውን የስኳር ጉድለት ለማሟላት ከውጭ ልናመጣ የነበረው በሀገራዊው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት የተነሳ ጥረታችን በፈለግነውና ባቀድነው ልክ አልተሳካም። እነዚህ ተደማምረው ነገሩን ረብሸውታል። በቅርቡ ፓርላማ ላይ ተነስቶ የነበረው ስኳር እጥረት ስለመኖሩ መግለፁ ነበር፤ አዎ እጥረት አለ።ግን በፍራንኮ ቫሉታ የገባ ስኳር አሁንም ገበያ ላይ አለ።ዋጋው ግን እስከ 70 ብር ነው። ትልቁ ችግር ስኳርን በግብዓት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች ሕብረተሰቡ በሚገዛው አነስተኛ ዋጋ መውሰድ ይፈልጋሉ።ስለዚህ ሽሚያ ይፈጠራል። አሁንም መጠኑ ቢያንስም በዝቅተኛ ዋጋ ለከተሞች ስኳር እያከፋፈልንና ለማቃመስ ጥረት እያደረግን ነው። ችግሩን በጊዜያዊነት ለማቃለል ፋብሪካዎች የሚነሱበት ወቅት ነው። ወንጂ ሥራ ጀምሯል። ኦሞ አካባቢ ያለውም እየተስተካከለ ነው። በተመሳሳይ ሌሎችም ሥራ ይጀምራሉ። በመሆኑም በጋውን የስኳር አቅርቦት ችግር አያጋጥምም። የስኳር አቅርቦት ችግር ሙሉ ለሙሉ ባይፈታም ማስተጋስ ይቻላል።ከውጭም በአንድ ወር ውስጥ ይገባል። ከውጭ ስኳር ለማስገባት አሁን መስመር ላይ ሁለት ሚሊዮን ስኳር አለ በአንድ ወር ውስጥ ይገባል፡፡

በዘላቂነት ለመፍታት የተጀመሩት ፋብሪካዎችና ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ስኳር በአቅማቸው ልክ እንዲያመርቱ ምን ያስፈልጋቸዋል፤ አሁናዊ ቁመናቸውስ ምንድን ነው፣ ነባር ፋብሪካዎቹስ ወደ ሙሉ አቅማቸው ለመድረስ ምን ያስፈልጋቸዋል የሚለውን የሚያሳይ የስትራቴጂ ፕላን ተዘጋጅቶ በሥራ አመራር ቦርድ እንዲፀድቅ ተደርጓል። የየፋብሪካዎቹም በየቦርዳቸው እንዲፀድቅ ተደርጓል። በዚህ መሰረት በ2020 ዓ.ም ስኳር ማምጣትን እናቆማለን ብለን እናስባለን፤ ለዚህም እየሰራን ነው። ለስኬቱ ደግሞ የሰው ኃይል ልማት፤ ፋብሪካና ፕሮጀክቶች ላይ መሥራት ይጠበቅብናል። በቀላሉ ውጤት አያመጣም፤ ግን የጀመርነው ሪፎርም ሥራም ለዚህ ያግዘናል። ሀገራዊ ሁኔታው መለወጡ እኛ ዘንድ ያለውን በእጅጉ ይለውጠዋል።

**አዲስ ዘመን፡-የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በፀጥታ ችግር በዚህ ደረጃ እየተፈተነ ባለበት ሁኔታ በፕራይቬታዜሽን የውጭ ባለሃብቶችን መሳብ አይከብድም?**

**አቶ ዘመድኩን፡-** እኛ ስትራቴጂክ እቅዳችን ስናወጣ ፋብሪካዎቹ እኛ እጅ ሆነው ቢቀጥሉ ብለን ነው።በዚህም 2020 ዓ.ም ግብን መሰረት አድርገን ስናስብ በመንግስት ቁጥጥር ሥር ቢሆኑ ብለን ነው።ስለዚህ ከፕራይቬታይዜሽ ጋር አይያያዝም፡፡በሁሉም ዘርፍ እየሰራን እንቀጥላለን፤ ችግሮቹን እየፈታን እንሄዳለን።

የሀገራችን ሁኔታ ፈጥኖ ከተተሻሻለና ባለሃብቶች ፈጥነው ከመጡ መንግስት በስኳር ኢንዱስትሪ ውስጥ ሁሉን ጠቅልሎ የሚሰራበት ሁኔታ የለም። በብዙ ሀገራት መንግስት ለስኳር ኢንዱስትሪ ድጋፍ ያደርግ ከሆነ እንጂ በግል የሚሰሩ ናቸው። በመሆኑም ይህ ተሞክሮ መምጣቱ ጥሩ ነው። ተወዳዳሪነት፣ ምርጥ ተሞክሮ፣ ቴክኖሎጂና በሌላው ዘርፍ ለውጥ ያመጣሉ። ስለዚህ እነርሱ ቢመጡ ውጤታማነታችን ይጨምራል። ከዚህ በፊት በነበረው የፕራይቬታዜሽን አካሄድ ትምህርት ስለተወሰደበት በመንግስት በኩል አስፈላጊ ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በመንግስት በኩልም የስኳር ፋብሪካዎችን «ፕራይቬታይዝ» ስማድረግ የጨረታ ሂደት ላይ ነው።የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ ደግሞ ፋብሪካዎችን በመምራት በ2020 ዓ.ም የስኳር ችግር እፈታስሁ ይላል።አካሄዳችሁ ከመንግስት አሠራርና ፍላጎት ጋር የተናበበ ነው ማስት ይቻላል?**

**አቶ ዘመድኩን፡-** ፍላጎታችን የተናበበ ነው። የ«ፕራይቬታዜሽን» ጉዳይ አሁን የመጣ አይደለም። መንግስትም «ፕራይቬታዜሽንን» ይፈልጋል።ዓለም ወደአንድ እየሄደች ስለሆነ እንደ ደሴት መነጠል አንችልም። እኛም በውጤታማነታችን ላይ ጥያቄ ይነሳበታል። የግሉ ዘርፍ ቴክኖሎጂ፣ አቅም፤ እውቀት አለው፤ ውድድሩ ፈጣን ነው። በመሆኑም ይህን ወስደን መንግስትም በሰጠን አቅጣጫ እየሠራ ይቆይ ነው። ዋጋው እየጨመረ ይሄዳል። አንድ የስኳር ፋብሪካ አንድ ትልቅ ከተማ ነው። ስለዚህ ይህን እየሠሩና እያስተካከሉ መሄድ ይገባል። እኛ ግን ከመንግስት የተለየ አቋም የለንም። ስለዚህ እየሰራችሁ ቆዩ በተባለው መሠረት እንሠራለን፤ ባለሃብቶች ሲመጡ ደግሞ መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ይተላለፋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ያስንበት ወቅት በስኳር ዘርፍ የቀውስ ወቅት ነው።በዚህ ወቅት ደግሞ ብልህ አመራር ይፈስጋል።እርስዎ በዚህ ወቅት የዚህም ተቋም አመራር በመሆንዎ ምን ይሰማዎታል።ከህዝቡ ጥያቄ አኳያ ጥሩ እንቅልፍ ይወስዶታል?**

**አቶ ዘመድኩን፡-** ከባድ ነው፤ ማለትም የትኛው መሥሪያ ቤት ቢሆንም፤ በተለይ እንደዚህ ለምግብ ፍጆታ የሚውል ነገር ማቅረብ ላይ ፈታኝ ነው።ዘይትም አንድ ወቅት እንደዚህ ፈታና ነበር።በእርግጥ መንግስት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች አሉ። ከውጭ ለማስገባት ስናወራ ከዶላር ውስንነት የተነሳ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ብዙ ናቸው።መድሃኒትና የመሳ ሰሉት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው። እንግዲህ ሥራው ፈታኝ ነው፡፡

እንቅልፍ ሲደክምህ ትተኛለህ እንጂ፤ ደስ ብሎህ አትተኛም። እጅህ ላይ በጣም አስቸኳይ ነገር ሲኖር ዘና ብሎ ለመተኛት በጣም ይቸግራል።ብዙ ተቋማት ተጨናንቀው ነው የሚሠሩት።የእኛ ዓይነቱና አቅርቦት ላይ የሚሠራ ደግሞ በእጥፍ እንደሚያጋጥመው መገመት አያዳግትም።በጣም በአስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ነው የምንሠራው።ዋናው ነገር የእኛ መጨነቅ ሳይሆን ስኳር ማቅረባችን ነው።ስኳር ከማቅረብ አኳያ አሁን በጋው ወቅት ላይ ስለደረስን ከችግሩ ወቅት ወጥተናል።በጣም አስጨናቂ ጊዜ አልፈናል፤ በአንድ ወር ውስጥ የተሻለ ነገር ይኖራል።

**አዲስ ዘመን፡- ስሰጡን ሰፊ ማብራሪያ በተቋማችን ሥም ከልብ አመሰግናስሁ፡፡**

**አቶ ዘመድኩን**፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡



ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## "የዲፕሎማሲ እልህ ምላጭ አያስውጥም"

**የጸሐፊውን ብዕር የቀሰቀሰው፤**

ቀደም ባሉት ሣምንታትና ቀናት ውስጥ የመላውን ዓለም መገናኛ ብዙኃን አየርና ገጾች ተቆጣጥሮ የሰነበተው በአሜሪካ የፖለቲካ መዘወሪያ ማዕከል በሆነው በዋሽንግተን ዲሲ ከታህሣሥ አራት ቀን ጀምሮ ለሦስት ተከታታይ ቀናት የተደረገው "የአሜሪካ አፍሪካ የመሪዎች ጉባዔ" ነበር። ጉባዔው በዋነኛነት እንዲካሄድ አዘጋጇን አሜሪካንን ግድ ያላት ወይንም የገፋፋት ሰበብ ምክንያት ምን እንደነበር በሀገሪቱ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ጋዜጣዊ መግለጫ በኩል የተገጸው እንዲህ ተብሎ ነበር።

"አሜሪካ ይህንን ጉባዔ ያዘጋጀችው የአፍሪካ አህጉር የጂኦ ፖለቲካ ሚና ከፍ ያለ መሆኑን ስለምታምን ብቻም ሳይሆን ዕውቅና ለመስጠት በማሰብም ጭምር ነው። የዓለማችንን ሁለንተናዊ መስተጋብር ለመቅረጽ አህጉረ አሜሪካ ትልቅ አቅም እንዳላት ሀገሬ አሜሪካ በሚገባ ትረዳለች። ስለዚህም ከአፍሪካ ጋር ለመሥራት ግድ የሆነው አስፈላጊያችን ብቻም ሳይሆን ግድ ስለሆነም ነው።"

በጉባዔው ላይ የተጋበዙት አርባ ዘጠኝ ያህል የአፍሪካ አህጉር ርዕሳነ ብሔሮችና የአፍሪካ ኅብረትን የወከሉ የልዑካን ቡድን አባላት ይህንን መሰሉን ምስክርነት ሲሰሙ ልባቸው ምን ያህል በደስታ እንደሚግል ለመገመት አይከብድም። "አያት ቅድመ አያቶቻችሁን በባርነት አፍልሰን አሜሪካን ዛሬ ለደረሰችበት ደረጃ እንድትበቃ ስላደረጉም ምሥጋና እናቀርባለን" የሚለው የፕሬዚዳንት ጆ. ባይደን ንግግርም ትርጉሙ ላቅ ያለ ብቻ ሳይሆን ንስሃ እንደማውረድም ተቆጥሯል።

ከጥናታዊ የግሪክ አማልክት መካከል አንዱ የነበረውና ዓላማችንን ለዘለዓለሙ በጫንቃው ላይ እንዲሸከም በብጤዎቹ አማልክት ግዞተኛ እንዲሆን ተፈርዶበታል ተብሎ እንደሚታመነው የተረት ተረቱ ዋና ገጸ ባህርይ እንደ አትላስ፤ ቀደም ብሎም ሆነ በጉባዔው መክፈቻ ላይ የተላለፈው መልዕክት የየግላቸውን ሀገር "በረከተ መርገም" በጀርባቸው ላይ አዝለው ለሚንገዳገዱት አፍሪካዊያኑ መሪዎቻችን ቀርቶ ለእኛ ለተራ ተገዢ ዜጎችም ቢሆን ከልብም ይሁን ከአፍ "የታላቅነት ዋነኛው ቁንጮ እኔ ነኝ" ከምትል ሀገር መሪዎች ይህንን መሰል ምሥክርነት መስማት እንደምን እንደሚያፍነከንክ "እኛን ሆኖ ማሰቡ" ብቻ በቂ ይሆናል።

የምሥክርነቶቹ ሁሉ የተስፋ "አዝመራ" በርግጥም በገቢር የሚለወጥ ከሆነና በተለይም "በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ውስጥ አፍሪካ በቋሚ አባልነት እንድትሳተፍ" ግፊት እንደሚያደርጉ በስብሰባው አጋፋሪ በአሜሪካው ፕሬዚዳንት የተሰጠው ማረጋገጫ በርግጡ ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ የአፍሪካ ጌቶቻችን "ዋንጫ ኖር! Cheers!" እያሉ መለኪያቸውን ቢያጋጩ ሀብታችን በግብዣ ባከነ ብለን ላንወቅሳቸው ቃል እንገባለን።

"ከጉባዔው የተገኘው ዝርዝር ፋይዳ ምንድን ነበር? ምንስ ጉዳት ያስከትላል? ወዘተ." ለሚሉት ጥያቄዎች ምልከታችንን በፈርጅ በፈርጁ እየተነተንን ለማጋራት ከጽሑፋችን ቢጋር እንዳያስወጣን በመስጋት እንጂ የጋባዧን ሀገር ድብቅ ፍላጎት፣ ግልጽ መሻትና የመሪዎቻችንን የልብ ትርታ ሳይቀር እየፈተሽን ብዙ ብዙ በተጨዋወትን ነበር።

"ኢትዮጵያስ ብትሆን ከጉባዔው ምን አተረፈች? ምንስ ተማረች?" ለሚለው እኛን ጠቀስ ስጋትና ጥያቄዎችም በዚህ ጽሑፍ ምላሽ አከል ሃሳቦችን አንሰነዝርም። ምክንያቱም የሰሞንኛውን የጉባዔ ጠበል ተቃምሰው የተመለሱት የልዑካን ቡድኑ አባላት በተደጋጋሚ "ከአግዋ እስከ ማእቀብ ማላላት፣ ከእርዳታ እስከ ሰፋፊ የብድር ተስፋ፣ ከፊት መጥቆር እስከ ፈገግታ" ስለተገኘው ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ኢኮኖሚያዊ ድርብ ድርብርብ ድል ተገቢውን ማብራሪያ ሲሰጡ ስለሰነበቱ "እንኳን ቀናችሁ፤ እንኳን ቀናን!" በማለት የተገኙት ትሩፋቶች ደጃፋችን ደርሰው እስኪታዩ ድረስ በትዕግሥት መጠበቁ ይበጃል። ከወዲሁ እየታዩ ያሉ አንዳንድ ምልክቶች አበረታች ስለመሆናቸውም አንክድም።

**"እልህ ምላጭ ያስውጣል"፡-** ለዲፕሎማሲ አይሠራም፤

ቀለም ዘልቆ ገብቷቸዋል የሚባሉት የሀገሬ ልጆችም ሆኑ (ልጆች ማለቴን ልብ ይሏል) የዕለት እንጀራቸውን ለማሸነፍ ሲጥሩና ሲግሩ የሚውሉት እኛን መሰል ሠርቶ በሌ ተራ ዜጎች የአሜሪካንንና የኢትዮጵያን ሰሞንኛ ቅርርብና መደናነቅ ሲሰሙ ምኞት ነስቶ እንደሚቆረቁራቸው ሲተቹና ሲቃወሙ ማድመጣችንንና ማንበባችንን አንዘነጋም። አንዳንድ "ወኔ ሙቅ" ምሁራንማ ከነጭራሹ "አሜሪካን መጣች ቀረች ምን ሊጎድልብን? ምንስ ሊሞላልን?" እያሉ በየሚዲያው ሲፎክሩ "ወይ እብደት!" እያልን በትዝብት ፈገግታ እንደሞሸለቅናቸው አላወቁ ከሆኑ ይወቁት። "ቻይና፣ ራሽያና ህንድን የመሳሰሉ ሀገራት ይኑሩልን እንጂ አሜሪካ መጣች ቀረች ኬሬዳሽ!" በማለትም "ምክረ ፍላጎታቸውን" አስረግጠው ለመንግሥት ሲገልጹ እያጉተመተምንም ቢሆን አድምጠናቸዋል።

በመሠረቱ "እልህ ምላጭ እንደሚያስውጥ" መዳፈር ወይንም "ለእልኸኛ ልጅ ቁርሱ ለእራት እንደሚቀመጥለት" ያለማወቅ ግትርነት እንጂ ትርፉ ምንም ነው። "እልኸኛ መዥገር ከቆዳ ጋር ተጣብቆ የሚሞተውም" ከአፈርኩ አይመልሰኝ በሚመስል የልብ ድንዳኔ በመጽናቱ ሳይሆን አይቀርም። ከመዥገር ጋር በቋንቋ መግባባት ስለማይቻል "ይሆን እንደሆን" በሚል ግምት ብሂሉን ለማስታወስ መገደዳችን አይዘንጋ።

እውነታው እንዲህ ነው፡- "በፖለቲካና በዲፕሎማሲ የዘላለም ጠላት ወይንም የዕድሜ ልክ ወዳጅ" የሚባል በደም የፀና ቃል ኪዳን የለም። ለወደፊቱም ይኖራል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም። ትናንት የሰላም ርግብን እድኜ ካልፈጀሁ እያለ ሲያቅራራ የነበረ አንድ መንግሥት፤ የዲፕሎማሲውና የፖለቲካው አካሄድ እንደሚጎዳውና አላዋጣ እንደሚለው ወይንም አልፎ አልፎ ሰብዓዊ ኅሊናው እየሸነቆጠ እንቅልፍ ሲነሳው ወዲያው መለስ ብሎ "ራሱን ልክ እንደ አበባ ምንጣፍ አንጥፎ ካልተረማመዳችሁብኝ" በማለት የመላዕክትን መሰል ክንፍ አቆጥቁጦ ልናስተውል እንችላለን።

እርግጥ ነው አሜሪካንን መሰል "ጡንቸኞች ነን" ባይ መንግሥታት ሰኞ ዕለት የንጉሥ ሳኦል እብሪት ተጣብቷቸው ያለምንም ምክንያት በንጹሐን ሀገራት ላይ ጦር ሲሰብቁ እንዳልዋሉ፤ በማግሥቱ ማክሰኞ የዳዊትን በገና ካልሰጣችሁንና ሰማያዊ ቅኔ ካልተቀኘን በማለት የኮሚክ ገጸ ባሕርያትን ሚና ተውሰው ቢተውኑ ሊገርመን አይገባም። በዲፕሎማሲ ውሏቸውም መልከ ብዙ ባሕርያቶቻቸውን (Double Face Jacket እንዲሉ) እያለዋወጡ ተውኔት ሊሠሩ ይችላሉ። አንዳንድ የፖለቲካ ሳይንስ በሳሎች እንዲህ መሰሉን የዲፕሎማሲ ግሪንቢጥ "The Joy Luck Club" በሚል ርእስ በሚታወቀው ዝነኛ የኮሚክ ድርሰቶች ይመስሉታል።

ስለዚህም ነው አምና "እርኩስ" ተብሎ የተብጠለጠለ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ውሳኔ ሳይውል ሳያድር እንደ "ቅዱስ" እየተቆጠረ እንዲካ ደምለት የሚፈለገው። በአጭሩ በዲፕሎማሲ መዝገበ ቃላት ውስጥ "ዘላለም" የሚለው ቃል ቤትኛ አይደለም። በዲፕሎማሲ ፖለቲካ አሠራር ውስጥ እልኸኝነት ቦታ የለውም። እልኸኛ ሀገርና መንግሥታት የሚተቹትም "የዱባ ጥጋብ ያለ ስንቅ ያዘምታል" እየተባለ ነው።

መንግሥታት "ረጅም ዘመናት ያስቆጠረ ወዳጅነት አዳብረናል" እያሉ የሚሸነጋገሉት በካሜራ ፊት ሲቆሙና ሲቀመጡ እንጂ በየጓዳቸው ውለው የሚያድሩት እንዴት አድርገን የፖለቲካውንና የዲፕሎማሲውን ልጓም ጨብጠን የፊት አውራሪነቱን ኮርቻ ልንቆናጠጥ እንችላለን እያሉ ነው። ሩቅ ማማተሩ ይቅርብንና ሀገራችን ከአሜሪካ ጋር ያለፈችበትን የቅርቡን ሁኔታና የዛሬውን ሁኔታ መለስ ብለን ብናስተውል ይህ እውነታ ፍንትው ብሎ ሊታየን ይችላል።

በራሷ ታዛ ሥር ብቻ ሳይሆን በተባበሩት መንግሥታት በርካታ ጉባዔዎችም ሳይቀር "ኢትዮጵያ በዚህና በዚያ" ምክንያት ካልተቀጣችና በማዕቀብ ካልተሸመደመደች እንቅልፍ አይወስደኝም እያለች እንዳልፎከረች ሁሉ ሰሞኑን በነበረው ጉባዔ ላይ "ጠብ እርግፍ" እያለች በክብሮትና በአንቱታ የልዑካን ቡድናችንን እንዴት ስታስተናግድ እንደባጀች ዐይተናል፤ ሰምተናል። እንዴት ሊሆን ቻለ? ከተባለ መልሱ "ዲፕሎማሲ ባህርይው ነው" ዋናው መልስ ነው። "የዲፕሎማሲ እልህ ምላጭ ላለማስዋጡም" ጥሩ ማሳያ ይሆናል።

"እንኳንም ከተዛተ፤ ከተወረወረም የሚታደግ አምላክ አለ" በሚል እምነቷ ኢትዮጵያ በጽናቷ እንደበረታች የዲፕሎማሲ የበላይነቱን የተቀዳጀችው በቀላሉ እንዳልሆነ በሚገባ ሊታወስ ይገባል። ተገዳዳሪዎቻችን ሲጮኹና ያዙን ልቀቁን እያሉ ሲፎገሉ ኢትዮጵያ በስንዴ እርሻዋ ላይ ተጠምዳ ነበር። በተንቆጠቆጠው የመንግሥታቱ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ በጋለ ትንፋሽ "ማዕቀብ ለመጣል ሲሟገቱብን" ሀገሬ የታላቁ ህዳሴ ግድቧን ሌት ተቀን ሳትል ግንባታውን ታጧጡፍ ነበር።

በአንድ እጇ የሉዓላዊ ክብሯን መመከቻ የጦር መሣሪያ፤ በሌላው እጇ የልማት ትጥቋን አጥብቃ ጠላቶቿን ስትፋለምና ልማቷን ስታጧጡፍ እያዩ እንዳልተዘባበቱባት ሁሉ ዛሬ ደርሰው ታላቅነቷን፣ ቃሏን ጠባቂነቷን፣ ለተፈራረመችው የሰላም ውል ተግባራዊነት ቁርጠኝነቷን፣ ለወደፊቷ ብሩህ አፍሪካ የብርሃን ፀዳል አከፋፋይ እንደምትሆን በአደባባይ ሲመሰክሩ ስናስተውል ሊገርመን አይገባም። ስለምን ቢሉ "ተግባር ከቃላት የበለጠ ስለሚከራከር ነው" ብለን "በዲፕሎማሲ ጥበብ" አሜንታቸውን ልናከብርላቸው ይገባል።

ይህ ዐምደኛ አንድም በሀገረ አሜሪካ በትምህርት ላይ በቆየባቸው ዓመታት የመንግሥ ታቸውን ሥርዓትና ባህርይ በቅርበት ለማወቅ በሚገባ ይተጋ ስለነበር፣ ሁለትም ከኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ አባላት እንደ አንዱ ሆኖ በበርካታ ሀገራት ጉብኝት ለማድረግና ከየመንግሥታቱ መሪዎች ጋር ለመወያየት ሀገሩ ዕድሉን አመቻችታለት ስለነበር የዲፕሎማሲን ተለዋዋጭ ባህርያትና አካሄድን የሚከታተለው በተለየ ፍላጎትና ቅርበት ነው።

ይህንን ጠነን ያለ ርዕሰ ጉዳይ ሊያዋዛ የሚችል አንድ ክስተት እናጋራ። ቀደም ተብሎ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ጸሐፊው በምድረ አሜሪካ በትምህርት ላይ እያለ እንደማንም የውጭ ሀገር ተማሪ ዩኒቨርስቲው በሚያዘጋጃቸው የባህል ልውውጥ መርሃ ግብሮች ላይ የራሱን ሀገር ማስተዋወቅ ይጠበቅበት ነበር።

እናም በአንድ ዝግጅት ላይ በዚያ አካባቢ የሚገኙ የሀገሩን ወንድም እህቶች ባህሉን እንዲያደምቁለት ትብብር ጠይቋቸው የየብሔረሰባቸውን አልባሳት ለብሰው እንዲመጡ አደራ አሸከማቸው። እነርሱም "እንኳንም ተጠይቀው ይቅርና በየምክንያቱም ቢሆን ሀገራቸውን ለማስተዋወቅ ይተጉ ስለነበር" ሴቶቹ የጋም እጀ ጠቢባን በተራቀቁበት የሀገር ልብስ፤ ወንዶቹም የየብሔረሰባቸውን አልባሳት ለብሰው በበዓሉ ላይ ልክ እንደ ከዋክብት ብርሃን እየተንቦገቦጉ የተዘጋጁበትን ትርዒት አቀረቡ።

የባህል ትርዒቱ እንደተጠናቀቀ ከግራ ከቀኝ የከበቧቸው ታዳሚዎች እንዲህ እያሉ በጥያቄ ያጣድፏቸው ጀመር፤ "እነዚህን አልባሳት የምትለብሱት በየትኞቹ በዓላቶቻችሁና ወራት ነው? በበረዶ ወራት የምትለብሱት ሌላ የተለየ የልብስ ዓይነት አላችሁ? በዓመት ስንት ቀናት ነው እነዚህን ልብሶች የምትለብሱት? ወዘተ." የተዥጎደጎዱት የጥያቄ ዓይነቶች ከ እስከ የሚባሉ አልነበሩም።

ለሁሉም ጠያቂዎች እንሰጥ የነበረው መልስ አንድና ተመሳሳይ ነበር። "እኛ የተለየ የበረዶ ወቅት የለንም። ከዓመት ዓመት እነዚህን ልብሶች መልበስ እንችላለን። አስቸጋሪ የምንለው የአየር ንብረት እምብዛም የለንም። በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል በየትኞቹም ወራትና በዓላት እነዚህ አልባሳት ይለበሳሉ" በማለት ልባችንን ትክት እስኪለው ድረስ ለጠያቂዎቻችን በሙሉ መልስ ሰጠን ስንጨርስ እንደተመካከሩ ሁሉ በአድናቆት እንዲህ ሲሉ መለሱልን።

"እናንተ ኢትዮጵያዊያን ለካስ በችግርም ሆነ በደስታችሁ ተረጋግታችሁ የምትኖሩት፣ በባህርያችሁም ቅብጥብጥነት የማይስተዋልባችሁ ተፈጥሮ በተረጋጋ መስመር ስላኖረቻችሁ ነው። ርሃብን በትእግሥት፣ ችግሮችን በመቻል፣ ጦርነታችሁንም በስክነት መርታችሁ በማሸነፍ የኖራችሁት ለካንስ ተፈጥሮ ገርታችሁ ነው። እኛ አሜሪካኖችማ እንደምታዩትና እንደምታውቁን በተፈጥሮ የአየር ንብረት እንደ እናንተ አልተባረክንም።"

"በክረምት ወቅት በረዶውና ቅዝቃዜው አይጣል ያሰኛል። የበጋው መክረርና ሙቀት መፈጠርን ያስጠላል። ጠዋት ብራ የመሰለው ከደቂቃዎች በኋላ በውሽፍር ዝናብ ሊጠቃ ይችላል። ሱናሚን መሰል አደጋዎች አብረውን የኖሩ መርገምቶች ናቸው። ስለዚህም የእኛ የአሜሪካ ዜጎች ባህርይ ልክ እንደ ተፈጥሮ ስክነት አይስተዋልበትም። ደስታችንም ሆነ ሀዘናችን አርቲፊሻልና የይምሰል ነው። አኗኗራችንም በለበጣ የተሸፈነ ነው። ከአለባበስ እስከ አመጋገባችን "ኦርጂናል" ብለን የምንለው ነገር እጅግም ነው።"

"እንኳንስ ማሕበራዊ አኗኗራችን ቀርቶ ፖለቲካችንንና ዲፕሎማሲያችንም ቅብጥብጥ ባህርያት ይስተዋልባቸዋል። ስክነት ይጎላቸዋል። አሜሪካ በዓለም ላይ የምትወስዳቸው በጎም ይሁን ክፉ ውሳኔዎችና እርምጃዎች ስሜታዊነት ያጠላባቸዋል። ረግተንና ሰክነን ለማሰብ ይህን መሰሉ ሥር የሰደደው ባህርያችን እድል አይሰጠንም። ችግሩ የተፈጥሮ ይሁን የማሕበረሰብ ሥሪታችን በሚገባ አላወቅነውም..." ሌላም በብዙ ጉዳዮች ዙሪያ መጨዋወታችንን አንዘነጋውም።

የአሜሪካ ፖለቲካና ዲፕሎማሲ ስክነት ጎሎት የሚቅበጠበጠው ምክንያቱ ከዚህ ጋር ይያያዝ ይሆን? የሀገሬ መሪዎችስ እንደተባለው በእርጋታና በማስተዋል የዲፕሎማሲውን የበላይነት ሊጎናጸፉ የቻሉት እንደተመሰከረልን የተፈጥሯችን ባህርይ አግዟቸው ይሆንን!? ለድምዳሜው ባንቻኮልም፤ አይሆንም ለማለቱም አንጣደፍም። የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ አካሄድ በርጋታ መመስገን ብቻም ሳይሆን፣ በሰፋ ዝግምተኛነቱም የሚወቀሰው ምናልባት ካነሳነው የባዕዳን ርዕሰ ጉዳይ ጋር ይገጣጠም እንደሆነ ጥናት ማድረጉና ደጋግሞ ማሰላሰሉ ክፋት ያለው አይመስለንም። ሰላም ይሁን።

## ንግድና ግብይት

# ዕድሎችን ይዞ የመጣው የቀረጥና ኮታ ነጻ እድል

**ፍሬሕይወት አወቀ**

**የኢትዮጵያ አምራቾች ከቻይና የቀረጥና ኮታ ነጻ እድል ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን በዋጋም ሆነ በምርት ጥራት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችላቸውን አቅም መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡ ቀረጡ መነሳቱ የውጭ ገበያ ፍላጎት በከፍተኛ መጠን እንዲጨምር ያደርጋል፤ የውጭ ገበያ ፍላጎት ከአገር ውስጥ ገበያ ፍላጎት በበለጠና በተሻለ ዋጋ የሚቀርብበት ነው። ከውጭ ገበያ የሚገኘው ገቢም የጥቅም ድርሻው ቢለያይም፣ አገሪቷን ጨምሮ በዘርፉ የሚገኙ ተዋናዮችን በሙሉ ተጠቃሚ ያደርጋል**

ኢትዮጵያ ምርቶቿን ከቀረጥ ነጻ ወደ ቻይና ገበያ ማስገባት እንድትችል የቻይና መንግሥት የሰጠውን እድል በአግባቡ ለመጠቀም በትኩረት እንደሚሰራ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በቅርቡ አስታውቋል። እድሉ ኢትዮጵያ 1 ሺ 644 የሚደርሱ የተለያዩ ምርቶችን ከቀረጥና ኮታ ነጻ ወደ ቻይና ገበያ ማስገባት የሚያስችል መሆኑንም ጠቁሟል።

የቻይና መንግስት ለኢትዮጵያ ምርቶች የቀረጥና ኮታ ነጻ እድል ሰጥቶ እንደነበር ያስታወሰው ሚኒስቴሩ፣ አሁን ደግሞ እድሉ ያካተታቸውን ምርቶች የሚጠቁም ዝርዝር ያካተተ ይፋዊ ፈቃድ መስጠቱን አስታውቋል። ሚኒስቴሩ ይህን ተከትሎም « በእጃችን ላይ ያሉ ምርቶችን በመላክና ተመርተው መላክ ያለባቸውን ምርቶችም እንዲመረቱ በማድረግ የተገኘውን እድል በአግባቡ ለመጠቀም እንደሚሰራ » አስገንዝቧል።

ከቀረጥና ኮታ ነጻ እድሉ ጋር በተያያዘ ያነጋገርናቸው የምጣኔ ሃብት ባለሙያው አቶ ክቡር ገና፤ ቀረጥ አንድ ዕቃ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ በታሪፉ መሰረት የሚፈጸም ክፍያ እንደሆነ ጠቅሰው፤ በተመሳሳይ ከቀረጥ ነጻ ሲባል ደግሞ ምንም አይነት ክፍያ የሌለው መሆኑን ይገልጻሉ። ቻይና የፈቀደችው ከቀረጥና ከኮታ ነጻ ገበያ ከዚህ ቀደም 20 ለሚደርሱ የአፍሪካ አገራት የተፈቀደ መሆኑን ያስታወሱት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፣ ያኔ ኢትዮጵያ እንዳልነበረችበት ተናግረዋል፤ ኢትዮጵያ የዚሁ ከቀረጥ ነጻ የገበያ ዕድል ተጠቃሚ እንድትሆን የተፈቀደላት በቅርቡ በሁለተኛ ዙር እንደሆነ ነው ያመለከቱት።

ኢትዮጵያ ምርቶቿን ከቀረጥና ኮታ ነጻ ወደ ቻይና ገበያ ማስገባት እንድትችል መፈቀዱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት አቶ ክቡር ይጠቁማሉ። እንደ እርዳታ የሚታይና ቻይና ከአፍሪካ ብሎም ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር እንደሚያስችልም ተናግረዋል። ይህን ተከትሎም ወደ ቻይና የሚገባው የምርት መጠን ቁጥሩ ከፍ እያለ ይመጣል ተብሎ እንደሚገመትም ጠቅሰው፣ እድሉ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ያደርጋል ሲሉ ይጠቁማሉ።

ያልተሸጡ የኢትዮጵያ ምርቶች ካሉ ወደ ቻይና ገበያ የሚገቡበት ዕድል እንደሚፈጥር ጠቅሰው፣ በተመሳሳይ አዲስና ተጨማሪ ምርቶች ማምረት ካስፈለገም እንዲመረቱና ምርትና ምርታማነትን እንዲያድግ ለማድረግ ሰፊ ዕድል እንደሚፈጥርም ነው ያስታወቁት።

እሳቸው እንዳሉት፤ ቻይና ከዚህ ቀደም 20 ለሚደርሱ የአፍሪካ አገራት በሰጠችው ከቀረጥ ነጻ ገበያ ዘጠኝ ሺህ የሚደርሱ የምርት አይነቶች ወደ ሀገሯ ገበያ እንዲገቡ ፈቅዳለች። ኢትዮጵያም ይህን ዕድል ማግኘቷ ከቡና በተጨማሪ ከዚህ በፊት ያልተመረቱና ወደ ውጭ ገበያ ያልተላኩ ምርቶችን የማምረትና የመላክ ዕድል እንደታገኝ ያስችላል።

በዋጋ ተመጣጣኝ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ በርካታ የምርት አይነቶች ከኢትዮጵያ ወደ ቻይና ገበያ እንዲገቡ ዕድል ይሰጣል። በተመሳሳይ ለውጭ ገበያ ቀርበው የማያውቁና ያልተመረቱ ምርቶችን በአዲስ መልክ ለማምረት ተነሳሽነትን ይፈጥራል።

በዚህ ከቀረጥ ነጻ ገበያ ውስጥ ዋናዎቹ ተዋንያን መንግሥትና የንግዱ ማህበረሰብ መሆናቸውን የጠቀሱት አቶ ክቡር፣ ይህ ዕድል በተለይ ለኢትዮጵያ የንግዱ ማህበረሰብ ጥሩ አጋጣሚን እንደሚፈጥር ያላቸውን እምነትም ተናግረዋል።

መንግሥት የውጭ ምንዛሪ እንደሚፈልገው ሁሉ ማህበረሰቡም ምርቱን አውጥቶ መሸጥ ይፈልጋል ሲሉ ገልጸው፣ ስለዚህ በአገር ውስጥ ያለው ምርት ወደ ውጭ ገበያ ወጥቶ መሸጥ እንዲችል ምርትና ምርታማነትን በስፋት ማሳደግ እንደሚያስፈልግም ያስገነዝባሉ። ከምርታማነት በተጨማሪም በጥራት አምርቶ ተወዳዳሪ በመሆን አገሪቷ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት እንድትችል ያግዛታል ሲሉ ያብራራሉ።

ሌላው የምጣኔ ሃብት ባለሙያ በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ‹‹ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)›› ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር ሞላ አለማየሁ ይህን ከቀረጥና ኮታ ነጻ እድል አስመልክተው ያነሱት ሃሳብም አቶ ክቡር ገና የጠቀሱትን ሃሳብ ያጠናክራል።

ቻይና አሁን የፈቀደችው ከቀረጥ ነጻ ገበያ ጠቀሜታው የጎላ እንደሚሆን እምነታቸው መሆኑን ገልጸዋል። የገበያ ፍላጎት በሌለበት ማምረት እንደማይቻል፣ የገበያ ፍላጎት ሲኖር ደግሞ በስፋት ማምረት እንደሚቻል አብራርተው፣ የአገሪቱ አምራቾች በዋጋም ሆነ በጥራት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ባለመሆናቸው ከቀረጥ ነጻ ገበያ መፈቀዱ ይጠቅማቸዋል ይላሉ። ለገበያው ሊያወጡ የሚጠበቅባቸውን ወጪ በከፍተኛ መጠን እንደሚቀንስላቸውም ይናገራሉ። ይህም ማለት ቀረጥ ተቀርጦባቸው ምርቶቻቸውን ወደ ቻይና ገበያ በሚያስገቡ አገራት ዋጋ የመሸጥ ዕድል ማግኘት ማለት ነው ሲሉ ገልጸው፣ በዚህም ኢትዮጵያ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችል ነው ያመላከቱት።

ዶክተር ሞላ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ከዚህ እድል በሚገባ ለመጠቀም ተወዳዳሪነቷን ከፍ ማድረግ ይጠበቅባታል። ጠቀሜታውን ዘላቂ ለማድረግም በአገሪቱ ያሉ አምራቾች ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

አምራቾቹን ፋይናንስን ከማቅረብ ጀምሮ በዘርፉ የተማረ የሰው ኃይል በማቅረብና ከልምድ ልውውጥ አንጻር በተለይም መንግሥት ሊደግፋቸው ይገባል ሲሉ ገልጸው፣ ከመንግሥት በተጨማሪም አምራቾችም የውስጥ አደረጃጀታቸውን አጠናክረው ተወዳዳሪ በመሆን ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ ገበያ መላክ አለባቸው። ተወዳዳሪ መሆን ሲችሉም ቀረጥ ኖረም አልኖረ የሚያሳስባቸው ችግር አይኖርም። ቀረጥ እያለም ተወዳዳሪ መሆን ይችላሉ ሲሉ ያብራራሉ።

ቀረጥ ለመክፈል ያወጡት የነበረውን ገንዘብ በምርትና ምርታማነት ማሳደግ ላይ ማዋል እንዳለባቸውም ዶክተር ሞላ አስታውቀው፤ በአቅም፣ በፋይናንስና አጠቃላይ በቴክኒክ ራሳቸውን እንዲያደራጁ ማድረግ አስፈላጊ ነው ይላሉ።

ዶክተር ሞላ ስጋታቸውንም አያይዘው ገልጸዋል። ከቀረጥ ነጻ በሆነው አግዋ ምርቶቻቸውን ለአሜሪካ ገበያ እንዲያቀርቡ ከተፈቀደላቸው ከሰሃራ በታች ከሚገኙ 38 አገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ እንደነበረች አስታውሰው፣ በዚህም የተለያዩ ምርቶችን ለአሜሪካ ገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ እንደነበረች ጠቅሰዋል። ኢትዮጵያ ከገበያው በመታገዷ በርካታ አምራቾች ሥራቸውን እንዲያቆሙ መገደዳቸውን ገልጸው፣ አገሪቷም የውጭ ምንዛሪ እንድታጣና የሥራ ዕድል እንዲቀንስ መሆኑን አንድ ችግር እንደሆነ ይናገራሉ።

ተወዳዳሪ ለመሆን መስራት እንደሚገባም ጠቁመዋል። ከቀረጥና ኮታ ነጻ ገበያ እድል አለ ብለው ለ10 እና 20 ዓመታት በዘርፉ ለውጥ ማምጣትና ተወዳዳሪ መሆን ካልቻሉ ቻይና የሆነ ጊዜ ላይ ከቀረጥ ነጻ ገበያውን ልክ እንደ አሜሪካ ሰርዣለሁ ብትል የአግዋ ገበያ አይነት ችግር ሊፈጠር እንደሚችል ነው ያስረዱት።

አቶ ክቡር ገናም ይህን የሚያጠናክር ሀሳብ ነው የሰጡት። ቻይና የፈቀደችው ከቀረጥ ነጻ ገበያ አሜሪካኖች በአግዋ የሚያደርጉት አይነት እንደሆነ ጠቅሰው፣ ይህ ውሳኔም የቻይና ውሳኔ እንደሆነና በተመሳሳይ ምርቱ ከአፍሪካ ወደ ቻይና ሲሄድ ነው እንጂ፤ ከቻይና ወደ አፍሪካ ሲመጣ የታክስ ቅነሳ ይደረጋል የሚል ስምምነት አለመኖሩን አስታውቀዋል።

ቻይና ለኢትዮጵያ የፈቀደችው ከቀረጥ ነጻ ገበያ ከአግዋ ጋር የሚመሳሰል መሆኑን አመልክተው፣ ከቀረጥ ነጻ የገበያ ዕድሉ በፈቃደኝነት ላይ ብቻ ተመስርቶ የተሰጠ በመሆኑ ዋስትናው የሚረጋገጥበት መንገድ አይኖርም ይላሉ። በስምምነት ላይ ሳይሆን በፍላጎት ብቻ የተመሰረተ ነውና፤ ዕድሉን የሰጠው አካል ነገ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ሊኖሩ ይችላሉ ያሉት አቶ ክቡር፣ ይህን እድል ወደ ህግና ስምምነት መለወጥ እንደሚያስፈልግም ነው ያመለከቱት። ወደ ህግና ስምምነት ከተለወጠም ዋስትና ሊሆን የሚችል የተሻለ ማረጋገጫ ሊኖር እንደሚችል ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አምራቾች በዋጋም ሆነ በምርት ጥራት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችላቸውን አቅም መፍጠር እንዳለባቸው ያብራሩት ዶክተር ሞላ፤ ቀረጡ መነሳቱ የውጭ ገበያ ፍላጎትን በከፍተኛ መጠን እንደሚጨምር ይገልጻሉ። የውጭ ገበያ ፍላጎት ከአገር ውስጥ ገበያ ፍላጎት በበለጠና በተሻለ ዋጋ የሚቀርብበት ነው። ከውጭ ገበያ የሚገኘው ገቢም የጥቅም ድርሻው ቢለያይም አገሪቷን ጨምሮ በዘርፉ የሚገኙ ተዋናዮችን በሙሉ ተጠቃሚ ያደርጋል ሲሉ አብራርተዋል።

ከመጨረሻው አምራች ጀምሮ ለውጭ ገበያ እስከሚያቀርበው አቅራቢ ድረስ ያሉ አካላት እያንዳንዳቸው የጥቅም ድርሻ ይኖራቸዋል ያሉት ዶክተር ሞላ፣ ለዚህም እያንዳንዳቸው ጥራት ያለውና የተሻለ ምርት ለማቅረብ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል ሲሉ ያስገነዝባሉ። ምክንያቱም ቀረጥ ተነሳ ማለት የጥራት መመዘኛዎቹ ተነሱ ማለት አይደለም በማለት ያብራሩት ዶክተር ሞላ፤ ከቀረጥ ነጻ የተፈቀደውን ዕድል ለመጠቀም አምራቾች በዋጋም ሆነ በጥራት ተወዳዳሪ ለመሆን በትጋት መሥራት የግድ እንደሚላቸው አመላክተዋል። በተለይም የቻይና ገበያ የሚፈልገውን የጥራት ደረጃ ለማሟላት በእሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ ተዋናይ የበኩሉን መወጣትና ብዙ መሥራት እንዳለበት ነው ያስረዱት።

ከፖሊሲና ከስትራቴጂ ጋር በተያያዘም አቅጣጫ በማሳየት ጭምር መንግሥት በዘርፉ ሰፊ ሥራ መሥራት እንዳለበት ጠቁመው፤ አምራቹን ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በማስተሳሰር ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንዳለበት ይጠቁማሉ። ለአብነትም የጥቅም ግጭት ቢፈጠር እንኳ በመንግሥት በኩል እንዴት መፈታት እንዳለበት የተመቻቸ ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል ነው የሚሉት።

በተለይም በቅንጅት በመሥራት ገበያው የሚፈልገውን ምርት በጥራት በማቅረብ ዕድሉን በተሻለ መንገድ ለመጠቀም ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ያላሰለሰ ጥረት እንደሚጠበቅ አመላክተዋል። ያ ካልሆነ ግን ኢትዮጵያ ከቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ ናት የሚል ስም ብቻ እንደሚተርፋት ያስገነዝባሉ።

እንደ ዶክተር ሞላ ማብራሪያ፤ የምርት ጥራትን ለማስጠበቅና ተወዳዳሪ ለመሆን ፋይናንስ ትልቅ ድርሻ አለው። በአገሪቱ የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት ካላቸው የፋይናንስ አቅም የተነሳ ለግብርናው ዘርፍ የተመቻቸ የብድር አገልግሎት አይሰጡም፤ ጥራት ያለው ምርት ለማምረትና ተወዳዳሪ ለመሆን አርሶ አደሩን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል።

እርግጥ ነው የግብርናው ዘርፍ በተፈጥሮ ላይ ጥገኛ በመሆኑ በዝናብ እጥረትም ሆነ በዝናብ ብዛት ስጋት አለበት። የፋይናንስ ተቋማት ቢሰጉም መንግሥት ትልቁን ድርሻ በመውሰድ ሊሠራበት ይገባል። የፋይናንስ ተቋማቱም አብዛኛው ህዝብ አርሶ አደር እንደመሆኑ የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን እሱ ላይ እምነት አሳድሮ መሥራትና ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አርሶ አደሩ ምርቱን ለውጭ ገበያ በጥራት ማቅረብ እንዲችል መሥራት ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ቡናን ጨምሮ ወደ ቻይና በምትልካቸው የምርት አይነቶች ብዛትና ጥራት ተወዳዳሪ በመሆን የዕድሉ ተጠቃሚ መሆን እንዳለባት አቶ ክቡር ያስገነዝባሉ፤ በተለይም ቻይና በዓለም ላይ እያደጉ ካሉ አገራት ቀዳሚውን ስፍራ የያዘች መሆኗን ጠቅሰው፣ ወደፊት የሚኖረው የገበያ ዕድል እጅግ ሰፊ መሆኑን ከግምት በማስገባት በርትቶና ጠንክሮ መሥራት አስፈላጊ መሆኑን አመላክተዋል።

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ከቀረጥ ነጻ ወደ ቻይና ገበያ እንዲገቡ ከተፈቀደላቸው ምርቶች መካከል እንደ በግ፣ ፍየል እና ግመል ያሉ የቁም እንስሳት እንዲሁም ስጋ እና የስጋ ውጤቶችና የተፈጥሮ ውሃ ይገኙበታል። እንደ ባቄላ እና ቦሎቄ ያሉትን ጨምሮ ጥራጥሬዎች፣ ሰሊጥ፣ ስንዴ (የስንዴ ዱቄት እንዲሁም ዱረም ስንዴን ጨምሮ)፣ በቆሎ እና አጃም ከቀረጥ ነጻ ዝርዝር ውስጥ መካተታቸው ተመላክቷል። ስኳር ድንች፣ አቮካዶ፣ ብርቱካን ሀባብ፣ የወይን ፍሬ እና ሌሎች ፍራፍሬዎችም ከቀረጥ ነጻ ፍቃድ ዝርዝር ውስጥ ይገኛሉ።

ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ በእጅ የተሰሩ አልባሳት እንዲሁም ከእንጨት እና ከቀርከሃ የተሰሩ የቤት እና የቢሮ መገልገያዎች ጭምር ኢትዮጵያ ከቀረጥ ነጻ ወደ ቻይና ገበያ ማስገባት እንድትችል ተፈቅዷል።

ቻይና ለኢትዮጵያ የፈቀደችው ከቀረጥ ነጻ የገበያ እድል በቻይና በኩል የተሰጠ ስለመሆኑ ሚኒስቴሩ የገለጸ ሲሆን፣ ከቀረጥ ነጻ ገበያው በኢትዮጵያ ላይ ምንም አይነት ግዴታን የማይጥል እንደሆነም አስታውቋል።

ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያን ቡና በመግዛት ከቀዳሚዎቹ ሀገራት ተርታ የተሰለፈችው ቻይና፤ ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያን ቡና በመቀበል 33ኛ ደረጃ ነበረች። በአሁኑ ወቅት ግን የኢትዮጵያን ቡና በመግዛት ቀዳሚ ከሆኑት ሀገራት ተርታ በመሰለፍ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ወደ ስምንተኛ ደረጃ መጥታለች።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ደግ ዓይኖች ፊትና ኋላ ናቸው

**ልጅአለም ፍቅሬ**



ቅን ልቦች በድቅድቅ ጨለማ እንደ አጥቢያ ኮከብ ያበራሉ፣ ብርሃናቸውም ለብዙኃኑ የሕይወት ስንቅ ነው። በጭላንጭሎቻቸው መንገድ ስተው ለሚያማትሩ መንገድ፣ ጎንበስ ላሉት ምርኩዝ፣ ለተቸገሩት እርዳትና ለመልካም ነገር ሁሉ አብነት ሆነው ይታያሉ፡፡ቅን ልቦች በእለት ከእለት እንቅስቃሴያቸው ፊትና ኋላ ቀኝና ግራቸውን በንቃት ይመለከታሉ፣ አንድም የምድሪቱን ሌላ ጊዜ ደግሞ የሰማዩን በማሰብ። ብቻ ጥሩ አልም የነገን ማን ያውቃል?

ለቅን ልቦች በሕይወት ውጤታማ መሆን ማለት ቁስ መሰብሰብ አይደለም። በእነርሱ ዘንድ ከቁስ ባሻገር የሀሳብ ልዕልናና ጥሩ የሕሊና እርካታ ወደር የሌለው ደስታ ምንጭ ነው። ቅን ልቦች እርዳታ በሚሹ ሰዎች ጫማ ውስጥ ቆመው መራመድ ይችላሉ፤ መልካም ለመሆን አዋቂ ወይም ጠቢብ ባለፀጋ ወይም ታዋቂ መሆን አይጠበቅባቸውም፣ ቀና ልብና በጎ ሕሊና መታደልን እንጂ። እኛ አወቅን ዘመንን ብለን ጉርብትናን፣ መረዳዳትን፣ መተሳሰብና የመቻቻል ባህላችን ገፍተን የኢትዮጵያዊነት መገለጫችንን አውልቀን ልንጥለው ስንታገል " አይ መዘመንማ እንዲህ አይደለም ወግ ልማዳችን፣ ሰብአዊነታችን ዘመን የማይሽረው የኢትዮጵ ያዊነታችን አብነት አድርገን በአብሮነት ተጋግዘን መኖር ነው እንጂ" ብለው በተግባር ያሳዩናል።

"ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን ነብር ዥንጉርጉ ርነቱን አይተውም" እንዲሉ ይህ ሁሉ ለእኛ የቆየ ወግና ልማዳችን ነው ብንል ማጋነን አይሆንብንም።ሰው በዘር በሐይማኖት ፤ በጎሳና በቋንቋ አጥር ታጥሮ በሚኖርበት በዚህ ዘመን ከሰብአዊነት አልፎ ለተጠማ ውሻ መራራትና ማሰብ አጀብ የሚያሰኝ በጎ ተግባር ነው።

ይህን ጉዳይ ለማንሳት ያነሳሳኝ ትዝብት ነገሩ እንዲህ ነው፣ ከዛሬ አስር ዓመት በፊት በአራዳ ክፍለ ከተማ አራት ኪሎ ወረዳ ዘጠኝ በተለምዶ ባሻ ወልዴ ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ለብዙ ዓመታት በቀበሌ ቤት በጉርብትና ይኖሩ የነበሩ ነዋሪዎች ቦታው ለልማት ተፈልጎ ወደ ሌላ ሰፈር ተዘዋወሩ። ይህ አጋጣሚ እዛው ሰፈር የሚኖሩ ውሾች ከባለቤቶቻቸው አለያያቸው። ባለቤት አልባ የሆኑት ውሾች ለከፋ ችግር ተጋለጡ፣ ታዛ አጥተው ጠዋትና ማታ ቁሩን ረፈድ ሲልም የፀሐይ ሐሩሩና የውሀ ጥሙ ተፈራርቆባቸው የተኮማተረ ጨርቅ መስለዋል። ታዲያ ይህንን ችግሮቻቸው አይተው በዝምታ ለማለፍ ያልመረጡት አባወራና እማ ወራ ችግሮቻቸው በጥቂቱም ቢሆን ለማቃለል አንድ በጎ ሀሳብ አመጡ። እሱም ትንሽ የውሀ መሙያ ጉድጓድ በኮንክሪት ማዘጋጀትና በየቀኑ ውሀ በመሙላት ቢያንስ ጥማቸውን ለመቁረጥ ቆርጠው ተነሱ። እንዳሰቡትም ሲሚንቶ ከበጎ ፈቃደኛ አግኝተው ለውሾቹ ውሃ መጠጫ አሰሩ። ይህን በጎ ተግባር እውን ያደረጉት ሰዎች አቶ ብርሀኑ ለማ እና ባለቤታቸው ወይዘሮ ዘሪቱ ተማም ይባላሉ። ሁለቱ ባለትዳሮች የቀበሌ ቤቶቹ ፈርሰው በዚሁ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ ወከማ ወደሚባለው ሰፈር ከመግባታቸው በፊት ባሻ ወልዴ ሰፈር ከ45 ዓመታት በላይ ኖረዋል ።መተዳደሪያቸውም በድሮው ሰፈራቸው መንገድ ጠረዝ ሸራ ወጥረው ሸቀጣ ሸቀጥ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የጀበና ቡና በመሸጥ ነው።

ባለትዳሮቹ ጠንካራ ሰራተኞች ናቸው። ከእሁድ በስተቀር ሁሌም ስራ ቦታቸው ላይ ስለማይጠፉ ባለቤት አልባ የሆኑት ውሾች ውሀ ሲጠማቸው ያስቸግሯቸዋል። አንዳንዴም እቃ ያበላሹባቸዋል፡፡ ታዲያ ይህንን ችግር በርህራሔ የተመለከቱት አባወራና እማወራ <<ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንዲሉ>> አንድም የውሾቹን መጠማትና መንከራተት በአዘኔታ ነበር ያዩት። በሌላ ጎኑ ደግሞ ከጤናቸው አንፃር ውሻ በተፈጥሮው ውሀ ሲጠማው የሚያስከትልበትን የጤና እክል እንዲሁም በሕብረተሰቡ ላይ የሚያመጣው መዘዝ የከፋ መሆኑን በመገንዘብ የውሀ ጉድጓድ አበጅተው እለት ከእለት ውሀ ተሸክመው እያመጡ ማጠጣትን ስራዬ ብለው ተያያዙት። በዚህ መልካም ተግባራቸው የተማረኩ የአካባቢው አንዳንድ ሰዎችም ውሀ እያመጡ ይሞሉላቸዋል፣ የአቶ ብርሀኑም የክትባት ጊዜያቸውን ጠብቀው ማስከተባቸውም ሌላኛው በጎ ምግባራቸው ነው፡፡እንስሳቱና አእዋፋቱም ተነጋግረው ቀጠሮ የያዙ ይመስል ሰዓታቸውን ጠብቀው በውሀ ጥም እንደ ቁርበት የተኮራመተውን ጉረሮቸው ለማረስረስ ዘወትር ወደ ገንዳው ይሄዳሉ።

ለመስጠትም መሰጠት ያስፈልጋልና ቀና አመ ለካከትና እርቀ አሳቢዎች ስንሆን መሠናክሎቻችንና ችግሮቻችን ለመልካም ሀሳባችን አጥር ሊሆኑብን አይችሉም።ይልቁንም መወጣጫ መሠላሎቻችንና የጥንካሬዎቻችን ምንጭ ይሆናሉ እንጂ። አንዳንዴ በጎ አሣቢ ስንሆን እራሳችንን ብቻ አይደለም የምንገነባው ቤተሰቦቻችን፣ ጎረቤቶቻችን ከፍ ሲልም የሀገርን ምሦሦ ነው የምንተክለው ።ከላይ ያየነው መልካም ምግባር ትንሽ ነገር መስሎ ሊታየን ይችላል፣ ነገር ግን የሚያመጣው በጎ ተፅዕኖ የጎላ ነው ።እንዲሁ እርቀን ብናስብ እንስሳት ገፀ በረከቶቻችን እንደሆኑ ይታወቀናል፣ አዳም የሚያስፈልገውን ሁሉም ነገር ተሟልቶለት በመጨረሻ ሲፈጠር አንዱ ስልጣን የተሰጠው እንስሳት ላይ መሆኑን ስንረዳ ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳላቸው ለማወቅ አያዳግትም፡ ፡እኛም ዛሬ እንስሳቱ፣ እፅዋቱ፣በአጠቃላይ ስነ ፍጥረታት ሁሉ የሕይወታችን ግማሽ አካል ናቸው፣ እውነት ለመናገር ግን ተፈጥሮን ማግባባትና ተላምዶ እንደመኖር የሚያስደስት ነገር የለም፣ ምክንያቱ ደግሞ ብንጠብቃቸው ብንከባከባቸው ይበልጥ ተጠቃሚዎቹ እኛው ነን።ያው መልካምነት መልሶ ሚከፍለው ለራስ ነው ይባል የለ? ለዚህም ደግሞ ከላይ ያየናቸው ባለታሪኮቻችን ትክክለኛ ማሳያዎች ናቸው፡፡

# ዓለም አቀፍ



## ታሊባን ጥፋት ፈጽመዋል ያላቸውን ሰዎች በግርፋት ቀጣ

በአፍጋኒስታን ሴቶችን ጨምሮ ከመቶ በላይ ጥፋተኛ የተባሉ ግለሰቦች በአደባባይ በግርፋት መቀጣታቸውን ታሊባን አስታውቋል።የታሊባን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሴቶችን ጨምሮ 122 ግለሰቦች በአገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል በስፖርት ስቴዲየም ውስጥ መገረፋቸውን ገልጿል።

በትዳር ላይ በመማገጥ፣ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር ግንኙነት በማድረግ፣ ከቤት አምልጦ በመጥፋት፣ ሌብነትና አደንዛዥ እጽ በማዘዋዋር በሚል ከ 25 እስከ 30 ግዜ መገረፋቸውን ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በመግለጫው አስታውቋል።የታሊባን መሪዎች የሻሪያ ሕግ በሃገሪቱ ተፈጻሚ እንዲሆን ባስተላለፉት ትዕዛዝ መሠረት የሞት ፍርድም ተፈጻሚ በመሆን ላይ ይገኛል።

ከሁለት ሳምንት በፊት በአገሪቱ ምዕራባዊ ግዛት በአደባባይ የተፈጸመው የሞት ቅጣት፣ "ሰውን የገደለ በሞት ይቀጣ" የሚለውን እስላማዊ ሕግ መሠረት በማድረግ ነው ተብሏል።የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ገለልተኛ ባለሙያዎች ቡድን በታሊባን እንደ አዲስ በመፈጸም ላይ ያለው ሕግ እያሳሰባቸው መሆኑን ባለፈው ሳምንት አስታውቀው ነበር። "ኢሰብዓዊና ክብርን የሚነካ" ያሉት ቅጣት በአስቸኳይ እንዲቆምም መጠየቃቸውን ቪኦኤ ዘገባ ያመለክታል።

ምንም እንኳን በታሊባን በግለጽ ባይጠቀስም የዚህም እስላማዊ ሕግ ትርጓሜ በሕዝብ ፊት ሰዎችን መግደልን፣ የሰውነት አካልን መቁረጥን እና በድንጋይ መወገርን የሚያጠቃልል ነው።ከፍተኛ መሪው የሰጡት ትዕዛዝ ታሊባን ባለፈው ዓመት ወደ ሥልጣን ከተመለሰ በኋላ ጥብቅ ሃይማኖታዊ ቅጣቶችን እና ሥርዓቶቹን እንደሚያላላ ቢገልጽም እየወሰዳቸው ያሉት እርምጃዎች ግን በተቃራኒው ሆነዋል።

በዚህም መሠረት ቅጣቶች በሃይማኖታዊው ሕግ እንዲሆኑ እንዲሁም ሴቶች ትምህርትን ጨምሮ ከተለያዩ ተግባራት እንዲታገዱ አድርጓል።ታሊባን እንደ አውሮፓውያኑ ከ1996 እስከ 2001 አፍጋኒስታንን በስተዳደረበት ወቅት በካቡል በሚገኘው ስታዲየም ሰዎችን በሕዝብ ፊት በመግረፍ እና በመግደል ተደጋጋሚ ውግዘት ይደርስበት ነበር።

## በሙስና ሲከሰሱ የነበሩት ሲሪል ራማፎሳ በኤኤንሲ መሪነታቸው እንዲቀጥሉ ተመረጡ

በሙስና ክስ ሲብጠለጠሉ የነበሩት እና በፓርቲያቸው መሪነት ላይ ጥያቄ የተነሳባቸው የደብብ አፍሪካው ፕሬዝዳንት ሲሪል ራማፎሳ በአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኤኤንሲን) መሪነታቸው እንዲቀጥሉ የመተማመኛ ድምጽ አገኙ።

ራማፎሳ ተፎካካሪያቸው የሆኑትን የቀድሞ የጤና ሚኒስትራቸው የነበሩትን ዝዌሊ ምኺዜን ያሸነፉት 2,476 ለ 1,897 በሆነ ድምጽ ነው።ፕሬዝዳንት ራማፎሳ የፓርቲው መሪነትን ያሸነፉት ባለፉት ሳምንታት ስማቸው በሙስና ሲነሳ ከሰነበተ በኋላ ነው። ተቀናቃኛቸውም በተመሳሳይ በሙስና የሚከሰሱ ቢሆንም ለመሪነት ቦታው ሲወዳደሩ ቀላል ያማይባል ድጋፍን አግኝተዋል። ሁለቱም ፖለቲከኞች ግን የሚቀርብባቸውን ክስ አይቀበሉትም።

ሲሪል ራማፎሳ በኤኤንሲ የመሪነት መንበር ላይ ለመቀጠል መመረጣቸው ከሁለት ዓመት በኋላ በሚካሄደው ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ላይ ለመወዳደር ቀዳሚ ቦታ ላይ ያስቀምጣቸዋል።ነገር ግን ራማፎሳ አሁንም ከቤታቸው ሶፋ ውስጥ በሌቦች ተዘርፏል ስለተባለው 580ሺህ ዶላር ምንጭ ጋር በተያያዘ በፖሊስ ምርመራ ይደረግባቸዋል እየተባለ ነው።

በአገሪቱ ፓርላማ አፈጉባኤ የተቋቋመው የሕግ ባለሙያዎች ቡድን ራማፎሳ ሕገ መንግሥቱን እና የፀረ ሙስና ሕግን በመጣስ ከሥልጣን የሚያስነሳ ክስ እንዲመሰረትባቸው ሃሳብ አቅርቦ ነበር።ነገር ግን ኤኤንሲ በፓርላማው ያለውን የበላይነት በመጠቀም የሕግ ባለሙያዎች ያቀረቡትን የውሳኔ ሃሳብ ውድቅ በማድረጉ ነው ለፓርቲው መሪነት የተወዳደሩት።የደቡብ አፍሪካው ፕሬዝዳንት ሲሪል ራማፎሳ የገዢው ፓርቲ መሪ ሆኖ ለመቀጠል ከዝዌሊ ምኺዜ ብርቱ ፉክክር ነው የገጠማቸው።

ፕሬዝዳንቱ ለገዢው የአፍሪካ ናሽናል ኮንግረስ (ኤኤንሲ) ፓርቲ መሪነት ጠንካራ ፉክክር የገጠማቸው ከሙስና ጋር በታያያዘ ሥልጣን እንዲለቁ ካስገደዷቸው ከቀድሞው የጤና ሚኒስትራቸው ዝዌሊ ምኺዜ ነው።



የቀድሞ የጤና ሚኒስትር በጆሃንስበግ በተካሄደው የፓርቲው ጉባኤ በመጨረሻዎቹ ሰዓታት ላይ ከፍተኛ ድጋፍ ለማግኘት ችለው ነበር ተብሏል።

ሁለቱ ዕጩዎች የኤኤንሲ መሪ ለመሆን እንዲችሉ 4 ሺህ 426 ተሳታፊዎች ከታደሙበት የፓርቲው ጉባኤ ድጋፍ ለማግኝት ተፎካክረዋል።

ራማፎሳ በግል የእርሻ ስፍራቸው ላይ ባለ ቤት ውስጥ የተሰረቀ የውጭ አገር ገንዘብ ሶፋ ስር ተገኝቷል መባሉን ለመሸፋፈን ሞክረዋል በሚል ክስ ከፓርቲው ጉባኤ በፊት ከሥልጣን እንዲለቁ ጫና እየተደረገባቸው ነበር።

በአገሪቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ በኩል የቀረበው ገለልተኛ ሪፖርት ራማፎሳ ሕግ ተላልፈው ሊሆን እንደሚችል አመልክተዋል። ሆኖም ፕሬዝዳንቱ የፈጸምኩት ነገር የለም ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# ረቡዕ ስፖርት





ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ለስፖርት ልማት ፈንድ ተግባራዊነት እንቅስቃሴ ይጀመራል

ብርሃን ፈይሳ



ለኢትዮጵያ ስፖርት እድገት ውስንነት ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ የገንዘብ ችግር ነው። በኢትዮጵያ ካሉ ከ31 በላይ የስፖርት ማህበራት መካከል የራሳቸው እውነንነቶች እንዳሉ ሆኖ በፋይናንስ ረገግ ራሳቸውን ችለዋል ተብለው የሚታሰቡት ሁለቱ(የአትሌቲክስ እና እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች) ናቸው። ስፖርት በባህሪው ከፍተኛ መዋዕለነዋይ የሚፈልግ ዘርፍ እንደመሆኑ እምቅ አቅሙ ያላቸው ስፖርቶች ሳይቀሩ ከገንዘብ እጥረት ጋር በተያያዘ እንቅስቃሴያቸው ሲገደብ ማየት የተለመደ ነው። በገንዘብ እጥረት ምክንያት የፈረሱ ክለቦችና ቡድኖች ጥቂት አይደሉም። ከዚህም አልፎ የዓለም አቀፍ ውድድሮችን የማዘጋጀት እድሎች ሲመክኑም ታይተዋል። አስፈላጊውን በጀት አጥተው ህልማቸው የከሸፈባቸው ስፖርተኞች ለዚህ አንድ ማሳያ ናቸው።

የኢትዮጵያ ስፖርት ሁሌም በበጀት እጦት እንደተፈተነ ነው። ዛሬም ይህ ፈተና ቀጥሏል። ለአብነት ያህልም የካራቴ ብሄራዊ ቡድን በገንዘብ እጦት ምክንያት የዓለም አቀፍ ውድድር ተሳትፎውን አቋርጦ መመለሱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በቦክስ ስፖርትም ኢትዮጵያ በሁለት ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ መሳተፍ ያልቻለችው ፌዴሬሽኑ የገንዘብ አቅም ስለሌለውና አስፈላጊው ድጋፍ ስላልተደረገለት ነው። በዚህም ስፖርተኞች የሚያገኙትን ልምድ እና ውጤት፣ ሃገርም ስሟ በውድድር መድረኮች የመጠራት አጋጣሚውን አጥተዋል። የችግሩ ተጽዕኖ ቀላል የማይባል በመሆኑም ስፖርቱ የተቋቋመበትን ዓላማም እስከማዛባት ሊደርስም ይችላል።

በኢትዮጵያ ስፖርት ውስጥ ለዘመናት ለኖረው ለዚህ ችግር ዘላቂ የሚሆነው መፍትሄ የስፖርት ልማት ፈንድ ነው። ይህ በበርካታ ሃገራት የሚተገበርና ውጤታማ የሆነ አሰራር በኢትዮጵያም ተግባራዊ መሆን እንደሚገባው በተደጋጋሚ ፡ ሃገራዊ የስፖርት ሪፎርም ጥናቱም ይህንኑ የሚጠቁም ሲሆን፤ ለስፖርት ልማት የሚውሉ አቅጣጫዎችን አስቀምጦ ገቢ በማሰባሰብ ስፖርቱን መደጎም እንደሚቻልም አስቀምጧል። ከጥናቱ ባለፈም በተለያየ ጊዜ በሚዘጋጁ መድረኮች እንዲሁም በብሄራዊ የስፖርት ምክር ቤት አባላትም ለሃገሪቷ ስፖርት እድገት መፍትሄ ሊሆን እንደሚችልም ተመላክቷል።

ስፖርትን የሚያስተዳድሩ አካላት ትልቅ ገንዘብ እንደሚያንቀሳቅሱ የሚታወቅ ሲሆን፤ ለውድድር፣ ለስልጠና፣ ለስፖርት ቁሳቁስ ግዢ፣ ለማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ ለባለሙያዎች ደመወዝ ወዘተ ብዙ ገንዘብ ያወጣሉ። ለዚህ የሚውለው የገንዘብ ምንጭም የተለያዩ ተቋማት፣ የመንግስት በጀት፣ ሎተሪ፣ ግብር፣ ብሄራዊ የስፖርት ተቋማት፣ ስፖንሰሮች፣ ስፖርተኞች፣ ክለቦችና በድጋፍ መልክ ይሰበሰባል። ይህም ኦሊምፒክን የመሳሰሉ ታላላቅ አለም አቀፍ ውድድሮች ሲመጡ ብቻ ተግባራዊ ሲደረግ ማየት የተለመደ ነው። ከዚያ ውጪ ባሉ ታላላቅ አለም አቀፍና ሌሎችም ውድድሮች በተለይም ከእግር ኳስና አትሌቲክስ ስፖርቶች በተጨማሪ ሌሎች ስፖርቶች ተጠቃሚ ሲሆኑ አይታይም።

ይህን ፈር ለማስያዝ አንዱ መፍትሄ ተደርጎ የሚቆጠረው ብሔራዊ የስፖርት ልማት ፈንድ ነው። በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ልማት ስራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ በቀለ፣ የስፖርት ልማት ፈንድ ማለት ከተለያዩ ምንጮች ሃብት በማሰባሰብና በአንድ ቋት እንዲገባ በማድረግ መጠቀም የሚቻልበትና በርካታ ሃገራትም የሚጠቀሙበት ዘዴ መሆኑን ይጠቁማሉ። ይህ አሰራርም በኢትዮጵያ ስፖርት ውስጥ የሚስተዋሉ ገንዘብ ነክ ችግሮችን መፍታት እንደሚችልም የሚናገሩት አቶ ተስፋዬ፣ በስፖርት ማህበራት ለሚነሱ የገንዘብ ጥያቄዎች በአፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት፣ በጀቱን ለማብቃቃት እንዲሁም ማህበራቱ ራሳቸውን እንዲያበቁ ለመደገፍም ሊውል እንደሚችልም ያብራራሉ።

ጉዳዩ በሀሳብ ደረጃ ከተነሳ የቆየ ቢሆንም በተለይ በዚህ ዓመት ወደ ስራ ለማስገባት በእንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝ አቶ ተስፋዬ ይጠቁማሉ። አቶ ተስፋዬ እንደሚናገሩት የስፖርት ልማት ፈንድን ተግባራዊ ለማድረግ እንደ ብሄራዊ ሎተሪ ካሉ ተቋማት ጋር ግንኙነት የተፈጠረ ሲሆን፤ የገቢ ምንጭ ይሆናሉ በሚል ከተቀመጡ አካላት በተወሰነ መልክ በዚህ ዓመት ለመስራት ታቅዷል። ይህንን ስራ ሊሰራ የሚችል ኮሚቴ ተዋቅሮም ወደ ስራ ገብቷል። ሙሉ ለሙሉ ወደ ስራ ሲገባም በስፖርት ማህበራቱ በኩል ለሚነሱ ቅሬታዎች በተወሰነ መልኩ መፍትሄ ይሆናል በሚል እንደሚጠበቅም ስራ አስፈጻሚው ያስረዳሉ።

ይህ የስፖርት ልማት ፈንድ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ ለስፖርት ማህበራት ድጋፍ በሚል ከገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ከሚመደበው በጀት እንደየስፖርት ዓይነቱ፣ የስፖርተኛ ብዛት እንዲሁም ከሚያስገኙት ውጤት አንጻር በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የሚደርሳቸው ይሆናል። ሌላው ደግሞ ዓለም አቀፍ ውድድሮች በሚካሄዱበት ወቅትም ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ድጋፍ ያደርጋል። በእርግጥ የስፖርት ህዝባዊው አደረጃጀት የተፈጠረው በራሱ ገቢ በማመንጨት ራሳቸውን እንዲችሉ ነው። ነገር ግን ከሃገር ገጽታ ግንባታ አንጻር ለተሳትፎ እንዲሁም ማበረታቻ ሽልማትን በልዩ ሁኔታ ድጋፍ ይደረጋል። ከስራው አስፈላጊነት አንጻር ሲታይ ግን ይህ ሁኔታ በቂ እና አርኪ ሊባል አይችልም። ሆኖም ከአዋጭነት አንጻር እየታየ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። ከግንባታ ጋር በተያያዘም የስፖርት ማህበራቱ በሚያቀርቡት ፕሮፖዛል መሰረት በጀቱን በማብቃቃት ድጋፍ ሊደረግ ይችላል።


## የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 03

በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን የእኖር ኤነር ወረዳ ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት በእኖር ኤነር መገር ወረዳ የከተማ ውሀ ለማስፋፋት የውሀ መስመር ለመዘርጋት የውሀ ፓይፖች/የቧንቧ እቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ግለሰቦች/ድርጅቶች ከዚህ በታች የተጠየቀውን መስፈርት ማሟላት አለባችሁ፡፡

**መስፈርት**

1. በዘርፉ ፈቃድ ያለውና የዘመኑ ግብር/ታክስ የከፈለና ፈቃዱን ያደሰ መሆን አለበት
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/TIN Numeber/ያለው
3. ቫት ተመዝጋቢ የሆነ እና
4. የጨረታ ማስከበሪያ የሚውል 20,000/ሃያ ሺህ ብር/ከባንክ የተረጋገጠ CPO ማቅረብ የሚችል በሙሉ በጨረታው መሳተፍ ይችላል፡፡ በጨረታው ለመሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱ ከእኖር ኤነር ወረዳ ፋ/ኢ/ል ጽ/ቤት ከግ/ን/አስ ስራ ሂደት 500/አምስት መቶ ብር ብቻ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ፡፡

ጨረታው አየር ላይ የሚቆየው ለተከታታይ ለ15 ቀናት ብቻ ሲሆን ጨረታው የሚከፈተው ደግሞ ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በ16ኛው/በአስራ ስድስተኛው ቀን ሲሆን ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሰነዱን ዋጋ ሞልተው በፖስታ በማሸግ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት የሚችሉ ሲሆን ጨረታው በዚሁ እለት ከቀኑ 6፡00 ታሽጎ 9፡00 ላይ ይከፈታል፡፡ የጨረታው መክፈቻ ቀን እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ ወደ ሚቀጥለው ቀን የሚቀየር መሆኑን እናሳስባለን፡፡

መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታው በሙሉ ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** የጨረታው አሸናፊ የሆነው ድርጅት እቃዎቹን እስከ ወረዳው ማእከል የሚያቀርብ ይሆናል፡፡

**አድራሻ፡-** እኖር ኤነር ወረዳ ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት

**ለበለጠ መረጃ፡-** 09,10,99,23,68 /09-45-46-75-13

**በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን የእኖር ኤነር ወረዳ ፋ/ኢ/ል ጽ/ቤት**



## ማስታወቂያ

ታምራት ደረጀ እምነበረድ አምራች በቤኒሻንጉል ክልላዊ መንግስት መተከል ዞን ቡለን ወረዳ ሞራና ኤኩሳቅ ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የእምነበረድ/ማዕድን ምርመራ ለማካሄድ በ 05/04/2015 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መ/ቤታችንን ጠይቀዋል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. | $36^0$ 02’ 38.84’’ E | $10^0$ 32’ 34,15’’ N |
| 2. | $36^0$ 02’ 40.85’’ E | $10^0$ 32’ 33,72’’ N |
| 3. | $36^0$ 02’ 41.27’’ E | $10^0$ 32’ 33,18’’ N |
| 4. | $36^0$ 02’ 43.23’’ E | $10^0$ 32’ 33,95’’ N |
| 5. | $36^0$ 02’ 45.13’’ E | $10^0$ 32’ 32,13’’ N |
| 6. | $36^0$ 02’ 46.97’’ E | $10^0$ 32’ 36,57’’N |
| 7. | $36^0$ 02’ 46.02’’ E | $10^0$ 32’ 38,89$^0$ N |
| 8. | 36◦ 02’ 46.28’’E | $10^0$ 32’ 40,15’’N |
| 9. | $36^0$ 02’ 47.57’’E | $10^0$ 32’ 40,34 ’’ N |
| 10. | $36^0$ 02’ 48.34’’E | $10^0$ 32’ 41,89 ’’N |
| 11. | $36^0$ 02’ 47.27’’E | $10^0$ 32’ 42,90 ’’N |
| 12. | $36^0$ 02’ 49.15’’E | $10^0$ 32’ 46,69 ’’N |
| 13. | $36^0$ 02’ 48.20’’E | $10^0$ 32’ 47,26 ’’N |
| 14. | $36^0$ 02’ 45.45’’E | $10^0$ 32’ 45,60 ’’N |
| 15. | $36^0$ 02’ 46.03’’E | $10^0$ 32’ 42,71$^0$ N |
| 16. | $36^0$ 02’ 43.72’’E | $10^0$ 32’ 40,41 ’’N |

**Block-1**

| | | |
|---|---|---|
| 1. | $36^0$ 02’ 50.66’’E | $10^0$ 32’ 40,65’’N |
| 2. | $36^0$ 02’ 52.41’’E | $10^0$ 32’ 40,04’’N |
| 3. | $36^0$ 02’ 54.99’’E | $10^0$ 32’ 41,79’’N |
| 4. | $36^0$ 02’ 55.61’’E | $10^0$ 32’ 39,25’’N |
| 5. | $36^0$ 02’ 58.37’’E | $10^0$ 32’ 40,19’’N |
| 6. | $36^0$ 02’ 59.15’’E | $10^0$ 32’ 42,21’’N |
| 7. | $36^0$ 02’ 56.35’’E | $10^0$ 32’ 43,21’’N |
| 8. | $36^0$ 02’ 56.20’’E | $10^0$ 32’ 44,79’’N |
| 9. | $36^0$ 02’ 53.50’’E | $10^0$ 32’ 44,90’’N |

ውስጥ በሚገኘው ቦታዎች ላይ ይገባኛል የሚል ቢኖር ይህ ማስታወቂያ በወጣ በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከነምክንያቱ ለኤጀንሲያችን እንዲያቀርቡ እናሳስባለን።

**በቤ/ጉ/ክ/መንግስት የማዕድን ሀብት ልማት ኤጀንሲ**


በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ